የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 25
ADDIS ABABA 4th February 2013


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ ዓ.ም

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ...... .......................................................ገጽ ፮ሺ፯፻፶፭


CONTENTS


Proclamation No. 780/2013

Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation.................................. Page 6755


## አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭

## በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት የደህንነት ስጋት ብቻም ሳይሆን የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ፣ ግልጽነት ያለው፣ ጤናማና ቀልጣፋ እንዳይሆን የሚያደርግ በመሆኑ፤

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመዋጋት በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥረት እየተደረገ በመሆኑ እና ኢትዮጵያም የዚህ ዓለም አቀፍ ጥረት አካል በመሆኗ፤

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 16.50


## PROCLAMATION No. 780/2013.

## A PROCLAMATION ON PREVENTION AND SUPPRESSION OF MONEY LAUNDERING AND FINANCING OF TERRORISM

WHEREAS, money laundering and financing of terrorism not only threaten security, but also compromise the stability, transparency, soundness and efficiency of the financial system;

WHEREAS, the effort to combat money laundering and financing of terrorism is being undertaken internationally and since Ethiopia is part thereof;

WHEREAS, it has become necessary to have a comprehensive legal framework to prevent and suppress money laundering and financing of terrorism;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

፩/ "በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ የተመለከተው ወንጀል ነው፤

፪/ "ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ የተመለከተው ወንጀል ነው፤

፫/ "የወንጀል ፍሬ" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከአመንጪ ወንጀል የተገኘ ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት ነው፤

፬/ "አመንጪ ወንጀል" ማለት ማንኛውም ለወንጀል ፍሬ ምንጭ የሆነና ቢያንስ አንድ ዓመት ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው፤

፭/ "ገንዘብ" ወይም "ንብረት" ማለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ሀብት ሲሆን በሀብቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም መኖሩን የሚያረጋግጥ እንደ ባንክ ክሬዲት፣ ትራቭለር ቼክ፣ የባንክ ቼክ፣ የክፍያ ትዕዛዝ፣ አክስዮን ወይም ቦንድ የመሰለ ማንኛውንም ዓይነት ሰነድ እና ከሀብቱ የተገኘን ወለድ፣ የትርፍ ድርሻ ወይም ሌላ ገቢን ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ይጨምራል፤

፮/ "የሽብርተኝነት ድርጊት" ማለት:-

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የተፈጸመ እ.አ.አ በ፲፱፻፺፱ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል በወጣው ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን አባሪ ከሆኑት ስምምነቶች በአንዱ የተፈጻሚነት ወሰንና ትርጓሜዎች የሚሸፈን የወንጀል ድርጊት፤

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No. 780/2013".

### 2. Definitions

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ "money laundering" means the offence as defined under Article 29 of this Proclamation;

2/ "financing of terrorism" means the offence as defined under Article 31 of this Proclamation;

3/ "proceeds of crime" means any fund or property derived or obtained, directly or indirectly, from a predicate offence;

4/ "predicate offence" means any offence capable of generating proceeds of crime and punishable at least with simple imprisonment for one year;

5/ "funds" or "property" means any asset, whether movable or immovable, or tangible or intangible, including legal instruments in any form evidencing title to or interest in such asset such as bank credits, traveler's cheques, bank cheques, money orders, shares, bonds, and any interest, dividend or other income or value generated by such asset;

6/ "terrorist act" means:

a) an act, whether occurring in Ethiopia or elsewhere, which constitutes an offence within the scope of, and as defined in one of the treaties listed in the annex to the 1999 International Convention for the Suppression of Financing of Terrorism;

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የተፈጸመ ከድርጊቱ ባህሪ ወይም ይዘት ሲታይ ህብረተሰቡን ለማስፈራራት ወይም መንግሥት ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት አንድን ድርጊት እንዲፈጽም ወይም እንዳይፈጽም የማስገደድ ዓላማ ኖሮት ሲቪል በሆነ የህብረተሰቡ አባል ላይ ወይም በውጊያ ሁኔታ ውስጥ ተሳታፊ ባልሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው ላይ ሞትን ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ለማድረስ ታስቦ የተፈጸመ ማንኛውም ሌላ ድርጊት፤

ሐ) በአዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩ አንቀፅ ፫ እና አንቀፅ ፬ ላይ የተደነገገው የሽብርተኝነት ድርጊት ትርጉምን ይጨምራል፤

፯/ "ሽብርተኛ" ማለት፡-

ሀ) በማንኛውም መንገድ፣ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ፣ ሕግን በመጣስና በራሱ ፈቃድ የሽብርተኝነት ድርጊት የሚፈጽም ወይም ለመፈጸም የሚሞክር፤

ለ) በሽብርተኝነት ድርጊት በአባሪነት የሚሳተፍ፤

ሐ) ሌሎች ሰዎች በሽብርተኝነት ድርጊት እንዲሳተፉ የሚያደራጅ ወይም አመራር የሚሰጥ፣ ወይም

መ) የሚያደርገው አስተዋፆ ሽብርተኝነትን እንዲያስፋፋ በመፈለግ ወይም ቡድኑ የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም ማሰቡን እያወቀ ለጋራ ዓላማ በቡድን የተሰባሰቡ ሰዎች ለሚፈጽሙት የሽብርተኝነት ድርጊት አስተዋፆ የሚያደርግ፤

በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የሚገኝ ማንኛውም ግለሰብ ነው፤

፰/ "የሽብርተኛ ድርጅት" ማለት፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የሚገኝ ወይም የሚንቀሳቀስ ሆኖ፡-

(፩) በማንኛውም መንገድ፣ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ፣ ሕግን በመጣስና በራሱ ፈቃድ የሽብርተኝነት ድርጊት የሚፈጽም ወይም ለመፈጸም የሚሞክር፤

b) any other act, whether occurring in Ethiopia or elsewhere, intended to cause death or serious bodily injury to a civilian, or to any other person not taking an active part in the hostilities in a situation of armed conflict, when the purpose of such act, by its nature or context, is to intimidate the population, or to compel government or an international organization to do or to abstain from doing any act;

c) including the definition of terrorist act provided under Article 3 and Article 4 of Proclamation No.652/2009;

7/ "terrorist" means any natural person, whether located in Ethiopia or elsewhere, who:

a) commits, or attempts to commit, terrorist act by any means, directly or indirectly, unlawfully and willfully;

b) participates as an accomplice in a terrorist act;

c) organizes or directs others to participate in a terrorist act; or

d) contributes to the commission of a terrorist act by a group of persons acting with a common purpose, where the contribution is made intentionally and with the aim of furthering the terrorist act or with the knowledge of the intention of the group to commit a terrorist act;

8/ "terrorist organization" means:

a) any group of persons, whether located or operating in Ethiopia or elsewhere, that:

(1) commits, or attempts to commit, terrorist act by any means, directly or indirectly, unlawfully and willfully;

(፪) በሽብርተኝነት ድርጊት በአባሪነት የሚሳተፍ፤

(፫) ሌሎች ሰዎች በሽብርተኝነት ድርጊት እንዲሳተፉ የሚያደራጅ ወይም አመራር የሚሰጥ፤ ወይም

(፬) የሚያደርገው አስተዋፅ ሽብርተኝነትን እንዲያስፋፋ በመፈለግ ወይም ቡድኑ የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም ማሰቡን እያወቀ ለጋራ ዓላማ በቡድን የተሰባሰቡ ሰዎች ለሚፈጽሙት የሽብርተኝነት ድርጊት አስተዋፅ የሚያደርግ፤

ማንኛውም ቡድን፤ ወይም

ለ) በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩ ድንጋጌዎች መሠረት በሽብርተኝነት የተሰየመ ድርጅት፤

ነው፤

፱/ "የፋይናንስ ተቋም" ማለት ባንክ፣ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሐዋላ ድርጅት ወይም ብሔራዊ ባንክ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የፋይናንስ ተቋም ብሎ የሚሰይመው ማናቸውም ሌላ ተቋም ነው፤

፲/ "ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ) የሪል ስቴት ወኪሎችንና ደላሎችን፤

ለ) የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶች ነጋዴዎችን፤

ሐ) የሚከተሉትን ለደንበኞቻቸው የሚያዘጋጁ፣ የሚፈጽሙ ወይም የሚያከናውኑ ጠበቆችን፣ ኖታሪዎችን እና ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎችን፡-

(፩) ሪል ስቴት መግዛትና መሸጥ፤

(፪) የደንበኛውን ገንዘብ፣ የገንዘብ ሰነዶችና ሀብት ማስተዳደር፤

(፫) የባንክ፣ የቁጠባ ወይም የገንዘብ ሰነድ ሂሳቦችን ማስተዳደር፤

(፬) ኩባንያ ለማቋቋምና ለማካሄድ ወይም ለመምራት የሚደረጉ መዋጮዎችን ማደራጀት፤ ወይም

(2) participates as an accomplice in terrorist act;

(3) organizes or directs others to commit terrorist act; or

(4) contributes to the commission of a terrorist act by a group of persons acting with a common purpose where the contribution is made intentionally and with the aim of furthering the terrorist act or with the knowledge of the intention of the group to commit a terrorist act;

or

b) an organization so proscribed as terrorist in accordance with the provisions of the Anti-Terrorism Proclamation No. 652/2009;

9/ "financial institution" means a bank, an insurance company, a micro finance institution, postal savings, money transfer institution or any other institution designated as such by the National Bank pursuant to the relevant law;

10/ "designated non-financial businesses and professions" include:

a) real estate agents and brokers;

b) dealers in precious metals or precious stones;

c) lawyers, notaries and other independent legal professionals when they prepare for, carry out or engage in transactions for their clients concerning:

(1) buying and selling of real estate;

(2) managing of client money, securities and other assets;

(3) management of bank, savings or securities accounts;

(4) organization of contributions for the creation, operation or management of companies; or

(፭) በሕግ የሰውነት መብት የሚኖራቸውን አካላት መመሥረት፣ ማካሄድ ወይም መምራትና የንግድ ተቋሚትን መግዛትና መሸጥ፤

መ) ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ የሂሳብ ባለሙያዎችን፤

ሠ) በማዕከሉ የሚሰየሙ ሌሎች የንግድና የሙያ ሥራዎችን፤

፲፩/ "ለፖለቲካ ተጽኖ የተጋለጠ ሰው" ማለት በማናቸውም አገር ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሃላፊነት የተሰጠው ወይም ተሰጥቶት የነበረ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ሲሆን የዚህን ሰው ቤተሰብ አባል ወይም ከዚሁ ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው ይጨምራል፤

፲፪/ "በቁጥጥር ሥር የሚደረግ ማስተላለፍ" ማለት የወንጀል ድርጊትን ለመመርመርና የድርጊቱ ተሳታፊዎችን ለመለየት ዓላማ፣ የወንጀል ፍሬን ወይም ሕገ ወጥ የሆነን ወይም የሚጠረጠር ሌላ ጭነትን ወይም ጥሬ ገንዘብን አግባብ ባላቸው ባለሥልጣናት እውቅናና ቁጥጥር ሥር ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲዘዋወር፣ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ፣ የኢትዮጵያን ግዛት አቋርጦ እንዲያልፍ ወይም ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ የመፍቀድ ስልት ነው፤

፲፫/ "ማገድ" ማለት የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ እንደተጠበቀ ሆኖ ገንዘብን ወይም ሌላ ንብረትን በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረትና ውሳኔው ጸንቶ ለሚቆይበት ጊዜ እንዳይተላለፍ፣ ወደ ሌላ እንዳይለወጥ፣ እንዳይወገድ ወይም እንዳይንቀሳቀስ መከልከል ነው፤

፲፬/ "መያዝ" ማለት ገንዘብን ወይም ሌላ ንብረትን በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረትና ውሳኔው ጸንቶ ለሚቆይበት ጊዜ እንዳይተላለፍ፣ ወደ ሌላ እንዳይለወጥ፣ እንዳይወገድ ወይም እንዳይንቀሳቀስ መከልከል እና በፍርድ ቤቱ በተሾመና ቁጥጥር በሚደረግበት ንብረት ጠባቂ ሥር እንዲተዳደር ማድረግ ነው፤

፲፭/ "መውረስ" ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የገንዘብ ወይም የንብረት ባለቤትነትን በቋሚነት ማሳጣት ነው፤

፲፮/ "የወንጀል መፈጸሚያ" ማለት በማንኛውም መንገድና በሙሉ ወይም በከፊል በዚህ አዋጅ የተደነገገ ወንጀል ወይም አመንጪ ወንጀል ለመፈጸሚያ የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ ማንኛውም ንብረት ነው፤

(5) creation, operation or management of legal persons and buying and selling of business entities;

d) independent accountants;

e) such other businesses and professions as may be designated by the Center;

11/ “politically exposed person” means any natural person who is or has been entrusted with prominent public functions in any country or in an international organization as well as a member of such person’s family or any person closely associated with him;

12/ “controlled delivery” means the technique of allowing proceeds of crime or other illicit or suspect consignment or cash to pass within, out of, through or into the territory of Ethiopia with the knowledge and under the supervision of the competent authorities, with a view to the investigation of an offence and the identification of persons involved therein;

13/ “freezing” means, without prejudice to Article 37 of this Proclamation, prohibiting the transfer, conversion, disposition or movement of funds or other property on the basis of, and for the duration of the validity of, a decision of the court;

14/ “seizure” means prohibiting the transfer, conversion, disposition or movement of funds or other property on the basis of, and for the duration of the validity of, a decision of the court and the administration of such funds or property by a receiver appointed and supervised by the court;

15/ “confiscation” means the permanent deprivation of ownership of funds or property based on the decision of the court;

16/ “instrumentality” means any property used or intended to be used in any manner, wholly or in part, to commit any offence stipulated under this Proclamation or a predicate offence;

፲፯/ "የወንጀለኞች ቡድን" ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የገንዘብ ወይም የሌላ ቁሳዊ ጥቅም በማግኘት ዓላማ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ከባድ ወንጀሎችን ለመፈጸም የተሰባሰቡና ተቀናጅተው የሚንቀሳቀሱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የያዘና ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የተደራጀ ቡድን ነው፤

፲፰/ "ተጠቃሚ የሚሆነው ባለቤት" ማለት ደንበኛን ወይም አንድን ሂሳብ በፍጹም ባለቤትነት የሚይዝ ወይም የሚቆጣጠር ግለሰብ፣ ግብይት በስሙ የሚካሄድለት ሰው ወይም አንድን በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል ወይም ከሕግ የመነጨ አደረጃጀትን ለመቆጣጠር ፍጹም ሥልጣን ያለው ሰው ነው፤

፲፱/ "ኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍ" ማለት ላኪ በሆነው ሰውና በፋይናንስ ተቋም አማካይነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚፈጸም በሌላ የፋይናንስ ተቋም ዘንድ ቀርቦ ክፍያውን ለሚቀበል ሰው ገንዘብ ማስተላለፍ ነው፤

፳/ "መዝገብ" ወይም "ሰነድ" ማለት ማንኛውም ዓይነት መረጃ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) ጽሑፍ የሰፈረበትን ማንኛውም ነገር፤

ለ) ሊተረጉመው ለሚችል ሰው መልዕክት የሚያስተላልፍ በማንኛውም ነገር ላይ ያለን ጭረት፣ ቁጥር፣ ምልክት ወይም ብስ፤

ሐ) በሌላ ነገር እገዛ ወይም ያለ እገዛ ድምፅ፣ ምስል ወይም ጽሑፍ ሊያወጣ ወይም ሊያሳይ የሚችልን ማናቸውም ነገር፤

መ) ካርታን፣ ፕላንን፣ ስዕልን፣ ፎቶን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ነገርን፤

ሠ) የኤሌክትሮኒክ ሰነዶችን፤

ረ) በሰው፣ በኮምፒውተር ወይም በሌላ መሣሪያ መነበብና መረዳት የሚቻል መረጃ የተመዘገበበትን ወይም ምልክት የተደረገበትን ማናቸውም ማቴሪያል፤

ሰ) ማንኛውም መረጃ በኮምፒውተር ውስጥ፣ በዲስክ ወይም በካሴት ወይም በማይክሮ ፊልም የተያዘ ወይም በማናቸውም መካኒካል ወይም ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ የተያዘ ማናቸውም መረጃ፤

17/ "organized criminal group" means a structured group of two or more persons, existing for a period of time and acting in concert with the aim of committing one or more serious offences, in order to obtain, directly or indirectly, a financial or other material benefit;

18/ "beneficial owner" means any natural person who ultimately owns or controls a customer or an account, the person on whose behalf a transaction is being conducted, or the person who ultimately exercises effective control over a legal person or arrangement;

19/ "wire transfer" means any transaction carried out on behalf of an originator person through a financial institution by electronic means with a view to making an amount of money available to a beneficiary at another financial institution;

20/ "record" or "document" means information of any kind, including the following:

a) anything on which there is a writing;

b) anything on which there is a mark, figure, symbol or perforation having meaning for persons qualified to interpret it;

c) anything from which a sound, an image or a writing can be produced, with or without the aid of anything else;

d) a map, plan, drawing, photograph or similar thing;

e) an electronic document;

f) any material on which data is recorded or marked and which is capable of being read or understood by a person, a computer or other device;

g) any information stored in a computer, disc or cassette or on microfilm or preserved by any mechanical or electronic device;

፳፩/ "ማዕከል" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፩/፪ሺ፩ የተቋቋመው የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ነው፤

፳፪/ "አግባብ ያለው ባለሥልጣን" ማለት ማዕከሉ፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ ወይም የምርመራ ሥራን በሃላፊነት የሚያከናውን አካል፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም የሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ነው፤

፳፫/ "ጥርጣሬ ያለበት ግብይት" ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፯(፩) የተመለከተው ግብይት ነው፤

፳፬/ "ከሕግ የመነጨ አደረጃጀት" ማለት በግልጽ የተሰጠ የባለአደራነት ወይም ሌላ ተመሳሳይ አደረጃጀት ነው፤

፳፭/ "ገንዘብ" ማለት የኢትዮጵያ ወይም የማንኛውም አገር የወረቀት ወይም የሳንቲም መገበያያ ነው፤

፳፮/ "ለአምጪው የሚከፈል ተላላፊ የገንዘብ ሰነድ" ማለት እንደ ቼክ፣ የመንገደኞች ቼክ፣ የተስፋ ሰነድ እና የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የመሰለ ለአምጪው የሚከፈል ወይም ያለገደብ በጀርባው ላይ ተፈርሞ የሚተላለፍ፣ ማንነቱ ለማይታወቅ ሰው እንዲከፈል የታዘዘ ወይም ሰነዱን በመስጠት ብቻ ሊተላለፍ በሚያስችል ማናቸውም ፎርም የታዘዘ የገንዘብ ሰነድ ሲሆን የክፍያ ትዕዛዙ ተፈርሞበት ሳለ የሚከፈለው ሰው ስም ግን ባለመጻፉ ጉድለት ያለበትን የገንዘብ ሰነድ ይጨምራል፤

፳፯/ "ድንበር ተሻጋሪ የባንክ አገልግሎት እና ተመሳሳይ ግንኙነት" ማለት በአንድ አገር ውስጥ ባለ ባንክ ሌላ አገር ውስጥ ላለ ባንክ አገልግሎት መስጠት ወይም በገንዘብ ተቋማት መካከል ለገንዘብ ሰነዶች ግብይት ወይም ለገንዘብ ዝውውር የሚደረግ ተመሳሳይ ግንኙነት ነው፤

፳፰/ "ደንበኛ" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

ሀ) የፋይናንስ ግብይት ወይም ሂሳብ የተዘጋጀለት፣ የተከፈተለት ወይም የተፈጸመለትን ሰው፤

ለ) የፋይናንስ ግብይት ወይም የሂሳብ ፈራሚ የሆነን ሰው፤

21/ "Center" means the Financial Intelligence Center established by the Council of Ministers Regulation No. 171/2009;

22/ "competent authority" means the Center, National Intelligence and Security Service, the police, public prosecutor or other investigative body, the Ethiopian Revenue and Customs Authority or any concerned regulatory authority;

23/ "suspicious transaction" means a transaction referred to in Article 17(1) of this Proclamation;

24/ "legal arrangement" means an express trust or other similar arrangement;

25/ "currency" means banknotes and coins of Ethiopia or any other country that are in circulation as a medium of exchange;

26/ "bearer negotiable instrument" means any monetary instruments such as cheques, traveler's cheques, promissory notes and money orders, that are either in bearer form, endorsed without restriction, made out to a fictitious payee, or otherwise in such form that title thereto passes upon delivery, and includes incomplete monetary instrument which is signed but with the payee's name omitted;

27/ "cross-border correspondent banking or similar relationship" means the provision of banking services by a bank in one country to a bank in another country, or a similar relationship between financial institutions for securities transactions or funds transfers;

28/ "customer" means including any of the following:

a) a person for whom a financial transaction or account is arranged, opened or undertaken;

b) a signatory to a financial transaction or account;

ሐ) ሂሳብ የተከፈተለትን ወይም በፋይናንስ ግብይት መብት ወይም ግዴታ የተሰጠውን ወይም የተላለፈለትን ሰው፤

መ) የፋይናንስ ግብይት እንዲፈጽም ወይም ሂሳብን እንዲቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠውን ሰው፤

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) ከተገለጹት ድርጊቶች መካከል አንዱን ለመፈጸም የሚሞክርን ሰው፤

ረ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ማንኛውንም ሰው፤

፳፱/ "ተጠቃሚ" ማለት ጥቅምን ወይም ትርፍን የሚያገኝ ወይም ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረትን እንዲቀበል የተሰየመ ሰው ነው፤

፴/ "ተቆጣጣሪ ባለስልጣን" ማለት የፋይናንስ ተቋማትን በሚመለከት ብሔራዊ ባንክ ሲሆን፣ እያንዳንዱን ፋይናንስ ነክ ያልሆነ የተሰየመ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ በሚመለከት ይህንኑ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ እንዲቆጣጠር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ነው፤

፴፩/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፴፪/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል::

## ክፍል ሁለት

## በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ስለመከላከል

### ፫. ጥሬ ገንዘብና ለአምጪው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን ድንበር አቋርጦ ስለማጓጓዝ

፩/ ማንኛውም ሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ የያዛቸውን ገንዘብ፣ ለአምጪው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶች፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት::

c) a person to whom an account or rights or obligations under a financial transaction have been assigned or transferred;

d) a person who is authorized to conduct a financial transaction or control an account;

e) a person who attempts to take any of the actions referred to from paragraph (a) to (d) of this sub-article;

f) any person as may be prescribed by regulation of the Council of Ministers;

29/ "beneficiary" means a person who receives benefits or profits, or is designated as the recipient of funds or other property;

30/ "regulatory authority" means the National Bank with respect to financial institutions and, with respect to each designated non-financial business or profession, a government organ empowered by law to regulate such business or profession;

31/ "person" means any natural or legal person;

32/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## PREVENTION OF MONEY LAUNDERING AND FINANCING OF TERRORISM

### 3. Cross-Border Transportation of Cash and Bearer Negotiable Instruments

1/ Any person who enters or leaves the territory of Ethiopia in possession of currency, bearer negotiable instruments, precious stones or precious metals shall declare same to the Ethiopian Revenue and Customs Authority when so requested.

፪/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገንዘብን፣ ለአምጪው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮችን ወይም የከበሩ ብረቶችን አስመልክቶ ሀሰተኛ መግለጫ የተሰጠ እንደሆነ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መግለጫ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ወይም ገንዘቡ፣ የክፍያ ሰነዶቹ፣ የከበሩ ድንጋዮቹ ወይም የከበሩ ብረቶቹ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል፣ የአመንጪ ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ውጤት ስለመሆናቸው ወይም ወንጀሉን ለመፈጸሚያ እንደሚውሉ ጥርጣሬ ሲኖር እነዚህኑ በሙሉ ወይም በከፊል የመያዝ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፫/ በጉምሩክ አዋጅ የዕቃ ውርስን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተያዘ ገንዘብን፣ የክፍያ ሰነድን፣ የከበረ ብረትንና የከበረ ድንጋይን በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፬/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተመለከተው ጥርጣሬ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለማዕከሉ ማቅረብ አለበት፡፡

**፬. በፋይናንስ ግብይቶች ሊኖር ስለሚገባው ግልጽነት**

የፋይናንስ ተቋማት፡-

፩/ በተመዘገበበት ወይም ፈቃድ ባወጣበት የውጭ አገር በአካል ከማይገኝና የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ውስጥ ከማይካተት ባንክ፣ ወይም

፪/ በተመዘገበበት ወይም ፈቃድ ባወጣበት የውጭ አገር በአካል የማይገኝና የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ውስጥ የማይካተት ባንክ ሂሳቦቹን እንዲጠቀምባቸው ከሚፈቅድ የፋይናንስ ተቋም፣

ጋር ድንበር ተሻጋሪ የባንክ አገልግሎት ወይም ተመሳሳይ የሥራ ግንኙነት ሊመሠርቱ ወይም የነበራቸውን ግንኙነት ሊቀጥሉ አይገባም፡፡

2/ The Ethiopian Revenue and Customs Authority shall have the power to seize part of or the whole amount of currency, bearer negotiable instrument or precious metals or precious stones in case of a false disclosure or a failure to disclose as required under sub-article (1) of this Article, or if there is suspicion of that all or parts of the currency, bearer negotiable instrument or precious metals or precious stones are proceeds or an instrumentality of money laundering, a predicate offence or financing of terrorism.

3/ The provisions of the Customs Proclamation relating the forfeiture of goods shall be applicable with respect to currency, bearer negotiable instruments or precious metals or precious stones seized under sub-article (2) of this Article.

4/ The Ethiopian Revenue and Customs Authority shall submit to the Center any information relating to the existence of suspicion referred to in sub-article (2) of this Article.

**4. Transparency in Financial Transactions**

Financial institutions may not enter into or continue a cross-border correspondent banking or similar relationship with:

1/ a bank that is registered or licensed in a foreign jurisdiction where it is not physically present and that is not affiliated with a regulated financial group subject to effective consolidated supervision in that jurisdiction; or

2/ a respondent financial institution in a foreign jurisdiction that permits its accounts to be used directly by a bank registered and licensed in a foreign jurisdiction but that is not physically present and is not affiliated with a regulated financial group subject to effective consolidated supervision in that jurisdiction.

## ፭. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላትን የሚመለከት ግልጽነት

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋሙና በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት ተጠቃሚ ስለሚሆኑት ባለቤቶቻቸውና ስለአመራር መዋቅራቸው የተሟሉ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎች መያዝ አለባቸው፡፡

፪/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን መረጃዎች ሲጠይቅ በተፋጠነ መንገድ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

## ፮. የደንበኞችን ማንነት ስለማጣራት

፩/ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን በመከላከልና በመቆጣጠር ዙሪያ ያሉትን ስጋቶች ለመለየት እና ለመመዘን አግባብ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡ እነዚህን ስጋቶች ለመመዘን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫(፩) መሠረት በማዕከሉ የሚሰጡ መረጃዎች ሙሉ በሙሉ ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተካሄደው የስጋት ምዘና እና ከዚሁ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ጠቃሚ ማስረጃና መረጃ በፅሁፍ፡ ተመዝግቦና ወቅታዊነቱ ተጠብቆ መያዝና በተፈለገ ጊዜ ለማዕከሉ፣ ለፖሊስ፣ ለዐቃቤ ሕግና የምርመራ ሥራን በሃላፊነት ለሚመራ አካል ተደራሽ መሆን አለበት፡፡

፫/ የፋይናን ስ ተቋም ወይም ፋይናንስ ነክ ያልሆነ የተሰየመ የንግድና የሙያ ሥራ፡-

ሀ) ከደንበኛ ጋር የንግድ ግንኙነት ከመመሥረቱ ወይም ሂሳብ ከመክፈቱ በፊት፤

ለ) በፋይናንስ ተቋሙ ዘንድ የባንክ ሂሳብ ከሌለው ወይም ፋይናንስ ነክ ካልሆነው የተሰየመ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ጋር የሥራ ግንኙነት ከሌለው እና፡-

## 5. Transparency of Legal Persons

1/ Legal persons established in Ethiopia shall maintain adequate, accurate and current information on their beneficial owners and control structure.

2/ The competent authority shall, upon request, have access to the information referred to in sub-article (1) of this Article in a timely fashion.

## 6. Identification of Customers

1/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions shall take appropriate steps to identify and assess their risks of money laundering and financing of terrorism. When conducting this risk assessment, any information provided by the Center under Article 13(1) of this Proclamation shall be fully taken into account.

2/ The risk assessment conducted under sub-article (1) of this Article and any underlying evidence and information shall be documented in writing, be kept up-to-date, and be readily available to the Center, the police, public prosecutor and the organ responsible to conduct investigation.

3/ A financial institution or a designated non-financial business or profession shall carry out customer due diligence measures:

a) before establishing business relations with or opening an account for a customer;

b) before carrying out a transaction for a customer who does not have an account or is not in an established business relationship with the financial institution or designated non-financial business or profession, and who wishes to carry out:

(፩) በአንድ ጊዜ ወይም የተያያዙ ሆነው በተለያየ ጊዜ ቢፈጸሙም ሲዳመሩ በማዕከሉ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ ግብይቶችን ለመፈፀም፤ ወይም

(፪) በአገር ውስጥ ወይም ወደ ውጭ በኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ለማስተላለፍ፤

ከሚፈልግ ደንበኛ ጋር ግብይት ከመጀመሩ በፊት፤

ሐ) ቀደም ሲል የተወሰደ የደንበኛ መረጃ ትክክለኛ ወይም የተሟላ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ሲፈጠር፤ ወይም

መ) በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን የሚመለከት ጥርጣሬ ሲኖር፤

የደንበኛን ማንነት ለማወቅ የሚያስችሉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ለ)(፩) የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በወቅቱ የማይታወቅ ከሆነ የደንበኛውን ማንነት የማጣራቱ እርምጃ የገንዘቡ መጠን እንደታወቀ ወይም ዝቅተኛው መጠን ላይ እንደደረሰ ወዲያውኑ መከናወን አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የደንበኞችን ማንነት ለማወቅ የሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

ሀ) የንግድ ግንኙነቱን ዓላማና ባሕሪ መረዳትንና መረጃ ማሰባሰብን፤

ለ) ገለልተኛ የሆኑ አስተማማኝ ምንጮችን፣ ሰነዶችን፣ ዳታዎችንና መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ደንበኛውን መለየትንና ማንነቱን ማረጋገጥን፤

ሐ) ተጠቃሚ የሚሆኑትን ባለቤቶች ማንነት መለየትን እና ይህንኑ ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድን፤

(1) a transaction above the amount fixed by the Center, whether conducted as a single transaction or several transactions that appear to be linked; or

(2) a transaction that is a domestic or international wire transfer;

c) whenever doubts exist about the veracity or adequacy of previously obtained customer due diligence information; or

d) whenever there is a suspicion of money laundering or financing of terrorism.

4/ If the amount of the transaction referred to in sub-article (3)(b)(1) of this Article is unknown at the time of the operation, the identification of customer shall be done as soon as the amount becomes known or the threshold is reached.

5/ Customer due diligence measures under sub-article (3) of this Article shall comprise the following:

a) understanding and collecting information on the anticipated purpose and intended nature of the business relationship;

b) identifying the customer and verifying the identity of the customer based on reliable independent source, documents, data or information;

c) identifying the beneficial owners and taking all reasonable measures to verify the identities of the beneficial owners;

መ) ደንበኛን ወክሎ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ከደንበኛው ውክልና የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥን እንዲሁም ማንነቱን መለየትንና ማረጋገጥን፤ እና

ሠ) በማዕከሉ የሚወሰኑ ሌሎች እርምጃዎች መውሰድን::

፮/ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ከደንበኞቻቸው ጋር የሚኖሩዋቸውን እያንዳንዱን የሥራ ግንኙነት ያለማቋረጥ በጥንቃቄ መከታተልና የሚፈጽሟቸው ግብይቶች ስለደንበኞቻቸው ካላቸው እውቀት፣ ከንግድ ሥራዎቻቸውና ከስጋት ደረጃዎቻቸው እና አስፈላጊ ሲሆን ከገንዘብ ምንጮቻቸው ጋር መጣጣሙን በትኩረት መመርመር አለባቸው::

፯/ የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች:-

ሀ) አዳዲስ አገልግሎቶችን፣ የአገልግሎት መስጫ ዘዴዎችንና አሠራሮችን በሥራ ላይ ከማዋል ወይም ለአዲስም ሆነ ነባር አገልግሎቶች አዳዲስ ወይም የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም ጋር ተያይዞ የሚመጡ በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ስጋቶችን መለየትና መመዘን፤ እና

ለ) እነዚህን ስጋቶች ለመቆጣጠርና ለመቀነስ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ፤

አለባቸው::

፰/ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች አንድ ደንበኛ ሊሆን የሚችል ወይም ደንበኛ የሆነ ወይም ተጠቃሚ የሚሆነው ባለቤት ለፖለቲካ ተጽና የተጋለጠ ሰው መሆን አለመሆኑን ለመለየት የሚያስችል አግባብ ያለው የስጋት መቀነሻ ዘዴ በሥራ ላይ ማዋልና እንደዚህ ዓይነት ደንበኛ ሲያጋጥም:-

ሀ) ከደንበኛው ጋር የሥራ ግንኙነት ከመመሥረቱ በፊት የከፍተኛ አመራር አባላት ፈቃድ እንዲገኝ ማድረግ፤

ለ) የደንበኛውን የሀብትና የገንዘብ ምንጭ ለማወቅ ተገቢ የሆነውን እርምጃ መውሰድ፤ እና

d) verify that any person purporting to act on behalf of a customer is so authorized, and identify and verify the identity of that person; and

e) taking other measures as prescribed by the Center.

6/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions shall exercise ongoing due diligence with respect to each business relationship and closely examine the transactions carried out to ensure that the transactions are consistent with the knowledge of their customer, the customer's commercial activities and risk profile and, where required, the sources of the customer's funds.

7/ Financial institutions and designated non financial businesses and professions shall:

a) identify and assess the risks of money laundering and financing of terrorism that may arise from the development of new products, delivery mechanisms and business practices, or from the use of new or developing technologies for both new and pre-existing products; and

b) take appropriate measures to manage and mitigate those risks.

8/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions shall have appropriate risk management systems to determine if a customer or a beneficial owner is a politically exposed person, and, if so:

a) obtain approval from senior management before establishing a business relationship with the customer;

b) take all reasonable measures to identify the source of wealth and funds of the customer; and

ሐ) ከደንበኛው ጋር በሚኖራቸው የሥራ ግንኙነት የተጠናከረና የማያቋርጥ ክትትል ማድረግ፤

አለባቸው፡፡

፱/ የፋይናንስ ተቋማት ድንበር ተሻጋሪ የባንክ አገልግሎትን እና ተመሳሳይ ግንኙነትን በተመለከተ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፫) እስከ (፮) ከተደነገጉት እርምጃዎች በተጨማሪ፡-

ሀ) የእያንዳንዱን ተቋም ሃላፊነት በግልጽ መረዳትና መመዝገብ፤

ለ) ግንኙነት የፈጠሩበትን የፋይናንስ ተቋም የሚመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰብ እና የሥራ ባህሪያቸውን በተሟላ ሁኔታ መረዳት፤

ሐ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ምርመራ የተካሄደበት መሆን አለመሆኑን ጨምሮ ለሕዝብ ይፋ በተደረጉ መረጃዎች ላይ ተመሥርቶ የፋይናንስ ተቋሙን መልካም ስም እና የሚደረግበትን የቁጥጥር ዓይነት መገምገም፤

መ) አዲስ ድንበር ተሻጋሪ የባንክ ግንኙነት ወይም ተመሳሳይ ግንኙነት ከመመሥረቱ በፊት የከፍተኛ አመራር አባላት ፈቃድ እንዲገኝ ማድረግ፤

ሠ) ግንኙነት የፈጠሩበት የፋይናንስ ተቋም በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን ለመከላከል በሥራ ላይ ያዋለውን የቁጥጥር ሥርዓት መገምገም፤ እና

ረ) በባንክ ሂሳብ አማካይነት ክፍያ የሚፈጸም ሲሆን ግንኙነት የፈጠሩበት የፋይናንስ ተቋም የባንክ ሂሳቡ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ደንበኞችን ማንነት ለማጣራት በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፫) እስከ (፮) እና በንዑስ አንቀጽ (፰) መሠረት የተደነገጉ እርምጃዎችን መውሰዱን እና በአስተላላፊ ተቋሙ ሲጠየቅም ሁሉንም የደንበኞች ማንነት መረጃዎች ማቅረብ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፤

አለባቸው፡፡

c) provide increased and ongoing monitoring of the business relationship with the customer.

9/ With respect to cross-border correspondent banking and similar relationships, in addition to the measures set out from sub-article (3) to (6) of this Article, financial institutions shall:

a) clearly understand and document the respective responsibilities of each institution;

b) collect information on and fully understand the nature of the respondent institution's business;

c) based on publicly available information, evaluate the respondent institution's reputation and the nature of supervision to which it is subject, including whether it has been subject to a money laundering or financing of terrorism investigation;

d) obtain approval from senior management before establishing a new cross-border correspondent banking or similar relationship;

e) evaluate the controls implemented by the respondent institution with respect to the prevention of money laundering and financing of terrorism; and

f) in the case of a payable through account, ensure that the respondent institution has carried out due diligence measures as set out from sub-article (3) to (6) and sub-article (8) of this Article on all customers having direct access to accounts of the correspondent institution, and is capable of providing all relevant customer due diligence information upon request to the correspondent bank.

፲/ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፫) እስከ (፱) የተመለከቱትን ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታዎቻቸውን ሊወጡ የማይችሉ ሲሆን የሥራ ግንኙነቱን መመሥረት፣ የባንክ ሂሣብ መክፈት ወይም ግብይት መፈፀም የለባቸውም፤ የንግድ ግንኙነት መስርተውም ከሆነ ማቋረጥ አለባቸው:: አግባብ ሆኖ ሲገኝም በዚህ አዋጅ መሠረት ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው::

፲፩/ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ በሚውልበት ወቅት ነባር የሆኑ ደንበኞችን በሚመለከት በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት የደንበኛ ማንነትን የማጣራት እርምጃዎች አግባብ ባለው ጊዜና ያለውን ተጨባጭ ሁኔታና ስጋት መሠረት በማድረግ የሚፈጸሙ ይሆናል::

፲፪/ የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድ እና የሙያ ሥራዎች ባልታወቀ ወይም የፈጠራ መሆኑ በግልጽ በሚታወቅ ስም የባንክ ሂሣብ መክፈት የለባቸውም::

## ፯. ማንነትን የመለየት ልዩ ግዴታ

፩/ የከበሩ ድንጋዮችና የከበሩ ብረቶች ነጋዴዎች በማዕከሉ ከተወሰነው መጠን በላይ የሆኑ ክፍያዎችን በጥሬ ገንዘብ ሲቀበሉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሠረት የደንበኞቻቸውን ማንነት መለየት አለባቸው::

፪/ የሪል ስቴት ወኪሎችና ደላሎች በሪል ስቴት ግዥና ሽያጭ ሲሳተፉ የተዋዋዮቹን ማንነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሠረት መለየት አለባቸው::

## ፰. የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን የሚመለከቱ ግዴታዎች

፩/ ሥራቸው የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን የሚጨምር የፋይናንስ ተቋማት የላኪውን ሙሉ ስም፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እና አድራሻ ወይም አድራሻ ከሌለ የዜግነት መታወቂያ ቁጥርን ወይም የትውልድ ዘመንና ቦታን እንዲሁም የተጠቃሚውን ስምና አድራሻ ወይም አድራሻ ከሌለ የዜግነት መታወቂያ ቁጥርን ወይም የትውልድ ዘመንና ቦታን እና ለማስተላለፉ ጥቅም ላይ የዋለውን የተጠቃሚውን የባንክ ሂሣብ ቁጥር መውሰድና ማጣራት አለባቸው:: መረጃው

10/ If a financial institution and designated non-financial business or profession cannot fulfill its obligations provided from sub-article (3) to (9) of this Article, it may not establish the business relationship, open the account or carry out the transaction, or shall terminate the business relationship. Where appropriate, a report shall be made to the Center in accordance with this Proclamation.

11/ For existing customers, at the time this Proclamation comes into force, customer due diligence measures under this Article shall be carried out at appropriate times, and based on materiality and risk.

12/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions may not keep anonymous accounts or accounts in obviously fictitious names.

## 7. Special Identification Requirements

1/ Dealers in precious metals and dealers in precious stones shall identify their customers in accordance with Article 6 of this Proclamation whenever receiving payment in cash in an amount more than the amount fixed by the Center.

2/ Real estate agents and brokers shall identify the parties, in accordance with Article 6 of this Proclamation when involved in transactions concerning the buying or selling of real estate.

## 8. Obligations Regarding Wire Transfers

1/ Financial institutions whose activities include wire transfers shall obtain and verify the full name, account number, and address, or in the absence of address the national identity number or date and place of birth of the originator of such transfers, as well as the full name and address, or in the absence of address the national identity number or date and place of birth of the beneficiary and the beneficiary account number where such an account is used to

በኤሌክትሮኒክ የማስተላለፍ መልዕክቱ ወይም የክፍያ ፎርሙ ውስጥ መካተት አለበት:: የባንክ ሂሳብ ቁጥር በማይኖርበት ጊዜ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፊያው ልዩ ማጣቀሻ ቁጥር እንዲይዝ ይደረጋል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት የፋይናንስ ተቋማት በኤሌክትሮኒክ ማስተላለፉ ሂደት በአቀባባይነት የሚሳተፉ ሲሆን እነዚህኑ መረጃዎች መያዝና አብረው ማስተላለፍ አለባቸው::

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች:-

ሀ) የክሬዲት ካርድ ወይም የዴቢት ካርድ ቁጥሩ አብሮ እስከተገለጸ ድረስ በክሬዲት ካርድ ወይም በዴቢት ካርድ አማካይነት የተፈጸመ ግብይትን ተከትሎ የተደረገ ማስተላለፍን፤ ወይም

ለ) ላኪውና ተቀባዩ ሁለቱም የፋይናንስ ተቋማት ሆነው በመካከላቸው የሚፈጽሙትን የገንዘብ ማስተላለፍ፤

በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆኑም::

፬/ የፋይናንስ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱ መረጃዎችን አሟልቶ ያልያዘ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍ ትዕዛዝ ሲያጋጥመው የማስተላለፍ ትዕዛዙን ተግባራዊ ማድረግ የለበትም::

፭/ ድንበር ተሻጋሪ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍ የሚሰጥ ወይም የሚቀበል ማንኛውም የፋይንናስ ተቋም ላኪውን ወይም ተቀባዩን በሚመለከት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚፈለጉ መረጃዎች የሚጎድሏቸውን የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፎች ለመለየት ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድና እንደ ስጋቱ መጠን የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፉን ለመፈጸም ወይም ለመቀበል፣ ውድቅ ለማድረግ ወይም ለማገድ እና መወሰድ ያለባቸውን የክትትል እርምጃዎች ለመወሰን የሚያስችል ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግ አለበት::

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ያልተሟላ የላኪዉን መረጃ የያዘ የድንበር ተሻጋሪ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን የስጋት መጠኑ ዝቅተኛ መሆኑን ወስኖ የተቀበለ የፋይናንስ ተቋም የተጠቃሚውን ማንነት ማጣራት አለበት::

process the transaction. The information shall be included in the message or payment form accompanying the wire transfer. If there is no account number, a unique reference number shall accompany the transfer.

2/ The financial institutions referred to in sub-article (1) of this Article shall maintain and transmit all such information when they act as intermediaries in a chain of payments.

3/ Sub-article (1) and (2) of this Article may not apply to:

a) transfers executed as a result of credit card or debit card transactions, provided that the credit card or debit card number accompanies the transfer resulting from the transaction; or

b) transfers between financial institutions where both the originator and the beneficiary are the financial institutions.

4/ A financial institution seeking to order a wire transfer that is unable to comply with the requirements under sub-article (1)of this Article may not execute the wire transfer.

5/ Any financial institution processing or receiving a cross-border wire transfer shall take reasonable measures to identify wire transfers that lack information on the originator or beneficiary as required under sub-article (1) of this Article and have in place risk based procedures to determine when to execute or receive, reject or suspend such a wire transfer and for determining any follow-up action required.

6/ A financial institution receiving a cross-border wire transfer that lacks complete originator information as required under sub-article (1) of this Article based on a determination of low risk shall verify the identity of the beneficiary.

፯/ በአሰራር የሚፈጠሩ የቴክኒክ ጉድለቶች የአገር ውስጥ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን አስመልክቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱ የላኪው ወይም የተቀባዩ መረጃዎች እንዳይተላለፉ ያደረጉ እንደሆነ ማስተላለፉን ያስፈጸመው ተቋም ከላኪው ወይም የማስተላለፉን ትዕዛዝ ከሰጠው ተቋም ያገኛቸውን መረጃዎች በሙሉ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

## ፱. <u>የተጠናከሩ ወይም ቀለል ያሉ የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰድ</u>

፩/ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡-

ሀ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ሊፈጸም ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት መኖሩ ሲታወቅ የተጠናከረ የደንበኞችን ማንነት የመለየት እርምጃዎች መውሰድ ይኖርባቸዋል፤ ወይም

ለ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ሊፈጸም የመቻሉ ስጋት ዝቅተኛ መሆኑ ሲታወቅ ቀለል ያለ የደንበኞችን ማንነት የመለየት እርምጃዎች መውሰድ ይችላሉ፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡-

ሀ) ውስብስብ የሆኑ ግብይቶችን፣ ባልተለመደ ሁኔታ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ግብይቶችን፣ ያልተለመዱ ሥርዓቶችን በመከተል የሚፈጸሙ ግብይቶችን እና በግልጽ ሊታይ የሚችል ኢኮኖሚያዊ ወይም ሌላ ሕጋዊ ዓላማ የሌላቸውን ግብይቶች፤ እና

ለ) በዓለም አቀፍ ደረጃ ክትትል እንዲደረግባቸው ጥሪ በቀረበባቸው አገሮች ውስጥ ከሚገኙ ወይም ከነዚሁ አገሮች ከመጡ ሰዎች ጋር የሚያደርጉትን የንግድ ግንኙነቶችና ግብይቶችን፤

በሚመለከት የተጠናከረ የደንበኞችን ማንነት የመለየትና የክትትል እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡

7/ Where technical limitations prevent the information on the originator or beneficiary under sub-article (1) of this Article to remain with a related domestic wire transfer, a record shall be kept by the processing institution of all the information received from the originator or the institution ordering the transfer.

## 9. <u>Enhanced or Simplified Due Diligence</u>

1/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions:

a) shall conduct enhanced customer due diligence measures in the case of identifying higher risk of money laundering or financing of terrorism; or

b) may conduct simplified customer due diligence measures in the case of identifying lower risk of money laundering or financing of terrorism.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, financial institutions and designated non-financial businesses and professions shall apply enhanced customer due diligence and monitoring measures:

a) to complex transactions, unusual large transactions, unusual patterns of transactions and transactions that have no apparent economic or other lawful purposes; and

b) to business relationships and transactions with persons from or in countries for which such measure is called for internationally.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)(ሀ) የተመለከቱት ግብይቶች መነሻ ምክንያቶችና ዓላማዎች በተቻለ መጠን ምርመራ ተካሂዶባቸው የተገኙት መረጃዎች በጽሁፍ ተመዝግበው መያዝ አለባቸው፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)(ለ) መሠረት የሚወሰዱ እርምጃዎች ውጤታማና ከስጋቱ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው፤ ማዕከሉም እነዚህኑ በተመለከተ የበኩሉን ተጓዳኝ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

## ፲. የመዝገብ አያያዝ

፩/ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች:-

ሀ) በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፮ እስከ አንቀጽ ፱ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የደንበኞችን ማንነት ከማጣራት እርምጃዎች የተገኙ የትንታኔ ውጤቶችን ጨምሮ የሂሳብ መዝገቦችን እና የንግድ መጻጻፎችን የንግድ ግንኙነቱ ካበቃበት ቀን አንስቶ ወይም ግብይቱ የተካሄደው ወይም የግብይት ሙከራ የተደረገዉ የንግድ ግንኙነት ካልመሠረተ ደንበኛ ጋር ከሆነ ግብይቱ ከተካሄደበት ወይም ከተሞከረበት ቀን አንስቶ፤ እና

ለ) የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን ጨምሮ የአገር ውስጥም ሆነ ድንበር ተሻጋሪ፣ የተሞከሩም ሆነ የተፈፀሙ ሁሉንም ግብይቶች የሚመለከቱ የተሟሉና የእያንዳንዱን ግብይት መረጃዎች መልሶ ለማየት የሚያስችሉ ዝርዝሮችን የያዙ መዝገቦችን ግብይቱ ከተፈጸመበት ወይም የግብይት ሙከራው ከተደረገበት ቀን አንስቶ፤

ቢያንስ ለአስር ዓመታት ያዘጡ ማቆየት አለባቸው፡፡

፪/ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተያዙ መዝገቦች ማዕከሉና ሌሎች አግባብ ያላቸዉ ባለሥልጣናት ሊያዩዋቸው እንዲችሉ ዝግጁ ሆነው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌዎች መዝገቦችን ለበለጠ ጊዜ ጠብቆ ስለመያዝ በሌሎች ሕጎች የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ተፈጻሚነት አያስቀሩም፡፡

3/ The background and purpose of the transactions referred to in sub-article (2)(a) of this Article shall be examined as far as possible and the finding be recorded in writing.

4/ The measures referred to in sub-article (2)(b) of this Article shall be effective and proportionate to the risks involved, and the Center may apply countermeasures in relation thereto.

## 10. Record-keeping

1/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions shall maintain:

a) copies of all records obtained through the customer due diligence measures provided from Article 6 to Article 9 of this Proclamation, and account files and business correspondence, including the results of any analysis undertaken, for at least ten years after the business relationship has ended, or, in case where a transaction is carried out for or attempted by a customer that is not in an established business relationship, from the date the transaction is carried out or attempted; and

b) records on all transactions, whether domestic or international, attempted or executed, including wire transfers, that are sufficiently detailed to enable the reconstruction of each individual transaction, for at least ten years from the date of the attempt or execution of the transaction.

2/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions shall ensure that records maintained pursuant to sub-article (1) of this Article are readily available to the Center and other competent authorities.

3/ The provisions of sub-article (1) of this Article may not affect the requirements under other laws to maintain records for longer period.

## ፲፩. የውስጥ የመከላከል ፕሮግራሞች

፩/ የፋይናንስ ተቋማት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮(፩) የተጠቀሱትን ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫(፩) መሠረት በማዕከሉ ተለይተው የተገለፁትን ስጋቶች ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመቆጣጠርና ለመቀነስ የሚያስችሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመከላከል የውስጥ ፖሊሲዎችና ቁጥጥሮች መዘርጋትና በሥራ ላይ ማዋል እንዲሁም የእነዚህን ፖሊሲዎችና ቁጥጥሮች አተገባበር መከታተልና አስፈላጊ ሲሆንም ማጠናከር አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሥራ ላይ እንዲውሉ የሚደረጉ ፖሊሲዎችና ቁጥጥሮች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው:-

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተጠቃሚ ባለቤቶችን ማንነት መለየትና ማረጋገጥን ጨምሮ የደንበኞችን ማንነት የመለየትና የማረጋገጥ እርምጃዎችን፣ ግብይት መከታተልን እና የማያቋርጥ የጥንቃቄ እርምጃ አወሳሰድ ሥርዓትን፤

ለ) የሕግ መከበርን ተገቢ በሆነ ቡድን ደረጃ የማረጋገጥ አመራር ሥርዓትን፤

ሐ) ከፍተኛ የብቃት ደረጃን ለማስጠበቅ የሚያስችል የተሟላ የሠራተኞች ምልመላ ሥርዓትን፤

መ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉ አጠራጣሪ ግብይቶችንና እንቅስቃሴዎችን ለመለየት የሚያግዙ ሥልጠናዎችን ጨምሮ ተከታታይ የሆኑ ሥልጠናዎችን ለሃላፊዎችና ለሠራተኞች መስጠትን፤

ሠ) የደንበኞችን ማንነት ለማጣራትና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ለመቆጣጠር የመረጃ ልውውጥ ደህንነትና አጠቃቀምን ጨምሮ መረጃዎችን በፋይናንስ ተቋማት መካከል ለመለዋወጥ የሚያስችል ስርዓትን፤እና

## 11. Internal Prevention Programs

1/ Financial institutions shall establish and implement internal policies and controls against money laundering and financing of terrorism that manage and mitigate effectively the risks identified under Article 6(1) or by the Center under Article 13(1) of this Proclamation, and monitor the implementation of such policies and controls and if necessary enhance them.

2/ The policies and controls to be implemented pursuant to sub-article (1) of this Article shall include:

a) customer identification and verification of identity measures, including identification and verification of beneficial owners, monitoring of transactions, and ongoing due diligence procedures in compliance with the requirements under this Proclamation;

b) appropriate group level compliance management arrangements;

c) adequate screening procedures to ensure high standards when recruiting employees;

d) ongoing training for officials and employees, including training to assist them in recognizing suspicious transactions and activities that may be linked to money laundering or financing of terrorism;

e) information sharing procedures within the financial group for purposes of carrying out customer due diligence measures and managing money laundering and financing of terrorism risks, including procedures to safeguard and use the information exchanged; and

ረ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወሰዱ እርምጃዎች መከበራቸውንና ውጤታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የውስጥ ኦዲት ሥርዓትን።

፫/ የፋይናንስ ተቋም ይህ አዋጅ በተቋሙ መከበሩን የማረጋገጥ ሃላፊነት ያለው ኦፊሰር በከፍተኛ አመራር ደረጃ መመደብ አለበት።

፬/ የፋይናንስ ተቋማት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ያወጧቸው ፖሊሲዎችና የቁጥጥር ሥርዓቶች በውጭ ያሉ ቅርንጫፎቻቸውንና በአብላጫ ባለቤትነት የያዟቸውን ተቋሞቻቸውን ጨምሮ በቡድን ደረጃ ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

፭/ ማዕከሉ ፋይናንስ ነክ ያልሆነ የተሰየመ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር በተያያዘ የሚኖረውን የስጋት ተጋላጭነትና የሥራውን ስፋት በማገናዘብ በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው ለእያንዳንዱ ግዴታ ምን ዓይነት እርምጃዎች መወሰድ እንደሚገባቸው መወሰን አለበት።

## ፲፪. ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች እና የሃይማኖት ድርጅቶች

ማንኛውም የሃይማኖት ድርጅት ወይም ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የስራው አካል አድርጎ ገንዘብ የሚሰበስብ፣ የሚቀበል፣ የሚሰጥ ወይም የሚያስተላልፍ ከሆነ ገንዘቡ ሽብርተኝነትን በገንዘብ ለመርዳት አለመዋሉን ወይም በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ጋር ያልተያያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ጋር በመተባበር አግባብነት ያለው አጠቃላይ ቁጥጥር በማዕከሉ ይደረግበታል።

f) internal audit arrangements to check compliance with and effectiveness of the measures taken in execution of this Proclamation.

3/ A financial institution shall designate a compliance officer at the senior management level to be responsible for ensuring its compliance with this Proclamation.

4/ Financial institutions shall be required to ensure that the policies and controls set out under sub-article (1) of this Article are applied on group wide basis, including by their foreign branches and majority-owned subsidiaries.

5/ The Center shall determine the types of measures that shall be taken by designated non-financial businesses and professions for each of the requirements in this Article, having regard to the risk of money laundering and financing of terrorism and the size of the business.

## 12. Non-Profit Organizations and Religious Organizations

Any religious organization or non-profit organization that collects, receives, grants or transfers funds as part of its activity shall be subject to appropriate oversight by the Center, in collaboration with the appropriate regulatory authority, to ensure that the fund is not misused for the purpose of financing of terrorism or associated with money laundering.

## ክፍል ሦስት

## በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ስለመከታተል

**፲፫. የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር**

ማዕከሉ በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

፩/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ስጋቶች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በዚህ አዋጅ መሠረት ይሰበስባል፣ ይቀበላል፣ ያከማቻል፣ ይመረምራል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

፪/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር በተያያዘ የሕዝቡ ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፤

፫/ በወን ጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን መነሻ፣ የአፈጸጸም ስልት፣ ዓይነት፣ ባህሪ እና አደጋ ያጠናል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም የመፍትሔ አቅጣጫ ይጠቁማል፤

፬/ የፋይናንስ ተቋማትን በመቆጣጠር ረገድ ለብሔራዊ ባንክ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ግዴታዎቻቸውን ለመወጣት የሚረዷቸው የአሠራር መመሪያዎችን ያወጣል፤

፭/ በዚህ አዋጅ መሠረት ያገኛቸውን በቀላሉ ለጉዳት የሚጋለጡና ሚስጥራዊ መረጃዎችን ለመጠበቅ የሚያስችል ተገቢ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ያቋቁማል፤

፮/ በአዋጁ መሠረት የተቀበላቸውን ሪፖርቶች፣ ለሕግ አስፈጻሚ አካላት የተመሩ ጉዳዮችን፣ ከተመሩት ውስጥ ምርመራ የተካሄደባቸውንና ክስ የተመሠረተባቸው የወንጀል ጉዳዮችን እና ዓለም ዓቀፍ ድጋፍ የተጠየቀባቸው ጉዳዮችን ጨምሮ ሥራውን በተመለከተ የተሟላ ስታትስቲክስ ይይዛል፤

## PART THREE

## DETECTION OF MONEY LAUNDERING AND FINANCING OF TERRORISM

**13. Powers and Duties of the Center**

The Center shall, without prejudice to its powers and duties specified under other provisions of this Proclamation:

1/ collect, receive, store, survey, analyze and disseminate information concerning suspected money laundering and financing of terrorism in accordance with this Proclamation;

2/ enhance public awareness and understanding of matters related to money laundering and financing of terrorism;

3/ conduct research relating to the source, mechanisms of commission, type, nature and dangers of money laundering and financing of terrorism and indicate solutions to the relevant bodies;

4/ without prejudice to the power of the National Bank to regulate financial institutions, issue guidelines to assist financial institutions and designated non-financial businesses and professions to comply with the obligations provided under this Proclamation;

5/ establish appropriate information management systems to ensure the protection of sensitive and confidential information disclosed to it under this Proclamation;

6/ maintain comprehensive statistics on its operations, including the number of reports received pursuant to this Proclamation, the number of referrals made to law enforcement bodies, the number of criminal investigations and prosecutions based on those referrals, and the number of international requests for assistance;

፯/ የደረሰው ሪፖርት ወይም መረጃ በማዕከሉ ግምገማ በዚህ አዋጅ ከተመለከቱት ወንጀሎች ውጭ ከሆነ ሌላ ወንጀል ጋር በተያያዘ ምርመራ ለማካሄድ ወይም ክስ ለመመሥረት የሚያስችል መሆኑን በበቂ ምክንያት ከጠረጠረ ጉዳዩን ወዲያውኑ አግባብ ላለው ሕግ አስፈጻሚ አካል ይመራል፤

፰/ የዚህን አዋጅ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ በራሱ ወይም ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣናት ጋር በመተባበር በፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ባልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ላይ ቁጥጥር፣ ፍተሻና ክትትል ያደርጋል፤

፱/ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ከመከላከል ጋር በተያያዘ ሌሎች ተቋማት የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲/ ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል።

## ፲፬. ከውጭ አገር መሰል ተቋማት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

፩/ ማዕከሉ ተመሳሳይ ተልዕኮ ካለውና ተመሳሳይ የሚስጥር አጠባበቅ ደረጃ ከሚከተል የሌላ አገር መሰል ተቋም ጋር በእንካ ለእንካ መርህ ላይ ተመሥርቶ የመረጃ ልውውጥ ሊያደርግ ወይም በሌላ መንገድ ሊተባበር ይችላል።

፪/ ማዕከሉ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም ዓላማ ከሌላው አገር መሰል ተቋም ጋር ስምምነት ሊፈራረም ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተገኘ መረጃ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን፣ አመንጪ ወንጀሎችን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ዓላማ ብቻ ይውላል።

## ፲፭. መረጃ ስለማግኘት

፩/ ማዕከሉ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገውን ተጨማሪ መረጃ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ካለበት ማንኛውም ሰው የማግኘት ሥልጣን ይኖረዋል።

7/ refer promptly to the appropriate law enforcement organ where, based on its analysis and assessment, there exists reasonable grounds to suspect that the report or information it has received is relevant to an investigation or prosecution of offence not covered under this Proclamation;

8/ either independently or in collaboration with the regulatory authorities, conduct inspections of financial institutions and designated non-financial businesses and professions to ensure compliance with this Proclamation;

9/ follow up the implementation and coordinate the actions of other governmental institutions combating money laundering and financing of terrorism;

10/ carry out other related activities.

## 14. Relations with Foreign Counterpart Agency

1/ The Center may, subject to reciprocity, share information or otherwise cooperate with any foreign counterpart agency that performs similar functions and is subject to similar secrecy obligations.

2/ For the purpose of sub-article (1) of this Article, the Center may enter into an agreement with the foreign counterpart agency.

3/ The information obtained pursuant to this Article shall be used only for the purposes of preventing and suppressing money laundering, predicate offences and financing of terrorism.

## 15. Access to Information

1/ The Center shall have the power to obtain from any person subject to the reporting obligation in accordance with Article 17 of this Proclamation any additional information it deems useful for the accomplishment of its functions.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚደረገው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪(፲)(ሐ) እና አንቀጽ ፲፯ (፪) የተደነገጉት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ነው::

፫/ ማዕ ከሉ ከደረሰው ሪፖርት ጋር ተያይዞ ለሥራው ያስፈልገኛል ብሎ የሚገምተውን ተጨማሪ መረጃ ከሚከተሉት አካላት ጠይቆ ማግኘት ይችላል:-

ሀ) ከፖሊስ ክፍሎች፤

ለ) ይህ አዋጅ የሚፈጸምባቸውን ሰዎች የመቆጣጠር ሃላፊነት ካለባቸው አካላት፤

ሐ) ከሌሎች የመንግሥት አካላት::

፬/ ማዕከሉ የሌላ አገር መሰል ተቋምን ጥያቄ መሠረት አድርጎ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) የተመለከቱትን መረጃዎች ማግኘት ይችላል::

**፲፮. ለተቆጣጣሪ አካላት ስለማሳወቅ**

ማዕከሉ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ግዴታዎቻቸውን እየተወጡ እንዳልሆነ ወይም ያልተወጡ መሆናቸውን ሲደርስበት ይህንኑ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ያሳውቃል::

**፲፯. ጥርጣሬዎችን ሪፖርት ስለማድረግ**

፩/ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ገንዘብ ወይም ንብረት የወንጀል ፍሬ ስለመሆኑ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዘ ወይም የተገናኘ ወይም ለዚሁ ተግባር ሊውል የሚችል ስለመሆኑ ሲጠረጥሩ ወይም ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖራቸው ወዲያውኑ ጥርጣሬያቸውን ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው:: ይህም ግዴታ ግብይት ለማድረግ የተፈጸመ ሙከራንም ይመለከታል::

፪/ ጠበቆች፣ ኖታሪዎችና ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች ደንበኞቻቸው ከሕግ አንፃር ሊይዙት የሚገባውን አቋም በመወሰን ሂደት ወይም በፍርድ ቤት ጉዳይ ወይም ከፍርድ ቤት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ደንበኞቻቸውን ደግፈው ከመከራከር ወይም ከመወከል እንዲሁም ወደ ክርክር እንዲገባ ወይም እንዳይገባ ምክር ከመስጠት ሃላፊነታቸው ጋር ተያይዞ የሚያገኟቸውን የደንበኞቻቸውን መረጃዎች ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አይኖርባቸውም::

2/ Sub-article (1) of this Article shall be applied subject to the restrictions provided under Article 2(10)(c) and Article 17(2) of this Proclamation.

3/ The Center may request in relation to any report it has received, any additional information it deems useful for the accomplishment of its functions from:

a) police departments;

b) authorities responsible for the supervision of the persons subject to this Proclamation;

c) other government organs.

4/ The Center may obtain the information referred to from sub-article (1) to (3) of this Article pursuant to a request received from a foreign counterpart agency.

**16. Disclosure to Regulatory Authorities**

Whenever the Center determines that financial institutions and designated non-financial businesses and professions are not complying or have not complied with the obligations set out in this Proclamation, it shall inform the relevant regulatory authorities accordingly.

**17. Reporting of Suspicions**

1/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions, that suspect or have reasonable grounds to suspect that funds or property are the proceeds of crime, or are related or linked to, or are to be used for financing of terrorism shall be required to submit promptly reports setting forth their suspicions to the Center. This obligation shall also apply to attempted transactions.

2/ Lawyers, notaries and other independent legal professionals shall have no obligation to report information they obtain on clients, in the course of determining the legal position for their clients or performing their tasks of defending or representing those clients in, or concerning judicial proceedings, including advice on instituting or avoiding proceedings.

፫/ ማዕከሉ ሪፖርቶች የሚቀርቡበትን ሥርዓትና ፎርም በመመሪያ ይወስናል፡፡

**፲፰. የጥሬ ገንዘብ ግብይትን ሪፖርት ስለማድረግ**

የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በአንድ ጊዜ ወይም የተያያዙ ሆነው በተለያየ ጊዜ ቢፈጸሙም ተዳምረው በማዕከሉ ከተወሰነው መጠን በላይ የሆኑ የጥሬ ገንዘብ ግብይቶችን ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡

**፲፱. ግብይትን ስለማዘግየት**

፩/ የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዘ ነው ብለው የሚጠረጥሩትን ግብይት ጥርጣሬያቸውን ለማዕከሉ ሪፖርት እስከሚያደርጉ ድረስ ከመፈጸም መቆጠብ አለባቸው፡፡

፪/ ግብይትን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከመፈጸም መቆጠብ የማይቻል ሲሆን ወይም ጥርጣሬውን ለማጣራት በሚደረግ ምርመራ ላይ እንቅፋት የሚፈጥር ሲሆን የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ግብይቱን ፈጽመው ጥርጣሬያቸውን ወዲያውኑ ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡

፫/ ማዕከሉ ከጉዳዩ ክብደት የተነሳ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አጠራጣሪ የሆነን ግብይት ከሦስት የሥራ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ እንዲታገድ ሊያዝ ይችላል፡፡

**፳. መረጃን አሳልፎ መስጠትን ስለመከልከል**

፩/ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፣ ዳይሬክተሮቻቸው፣ ሃላፊዎቻቸውና ሠራተኞቻቸው፡-

ሀ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ጥርጣሬን የሚመለከት መረጃ ለማዕከሉ ሊሰጥ መሆኑን ወይም በመስጠት ላይ ወይም የተሰጠ መሆኑን፣ ወይም

3/ The Center shall issue directive on the procedures and form in which reports shall be submitted.

**18. Cash Transaction Reporting**

Financial institutions and designated non-financial businesses and professions shall report to the Center cash transactions above the amount fixed by the Center, whether conducted as a single transaction or several transactions that appear to be linked.

**19. Postponing of Transactions**

1/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions shall refrain from carrying out transactions which they suspect to be related to money laundering or financing of terrorism until they have reported their suspicion to the Center.

2/ Whcre refraining from carrying out transactions in accordance with sub-article (1) of this Article is impossible or is likely to frustrate the efforts to investigate suspected transactions, the financial institutions and designated non-financial businesses and professions shall execute the transactions and report their suspicions to the Center immediately afterwards.

3/ If, by reason of the seriousness of the case, the Center considers it necessary, it may order the suspension of a suspicious transaction for a period not to exceed three working days.

**20. Prohibition of Tipping-off**

1/ Under no circumstance shall financial institutions and designated non-financial businesses and professions, their directors, officers and employees disclose to their customers or third parties that:

a) information concerning suspected money laundering or financing of terrorism will be, is being or has been provided to the Center; or

ለ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ምርመራ ሊካሄድ መሆኑን ወይም በመካሄድ ላይ ወይም የተካሄደ መሆኑን፣

የሚመለከት መረጃ ለደንበኞች ወይም ለሦስተኛ ወገኖች በምንም ሁኔታ መስጠት የለባቸውም።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌዎች በፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ዳይሬክተሮች፣ ሃላፊዎች፣ ሠራተኞችና የሕግ አማካሪዎች እና አግባብ ባላቸው ባለሥልጣናት መካከል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ጥርጣሬን የሚመለከት መረጃ መግለጽን ወይም መለዋወጥን የሚከለክሉ አይሆኑም።

## ፳፩. በጥርጣሬ ሪፖርት ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ

ማዕከሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረው የሚመለከተው ወንጀል መርማሪ አካል በቀጣይ ስለሚወሰደው እርምጃ እንዲወስን አግባብ ያለውን መረጃ ያስተላልፍለታል።

## ፳፪. የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች ሥልጣንና ተግባር

፩/ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ግዴታዎች አክብረው መሥራታቸውን መቆጣጠር አለባቸው።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች:-

ሀ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን፣ አመንጪ ወንጀሎችን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በመመርመርና በመክሰስ ረገድ ከሌሎች አግባብ ካላቸው ባለሥልጣኖች ጋር ይተባበራሉ፣ መረጃ ይለዋወጣሉ፤

ለ) በውጭ አገር የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት ቅርንጫፎችና የአብዛኛው አክስዮን ባለድርሻ የሆኑባቸው ተቋማት የአገሩ ሕጎች እስከፈቀዱ ድረስ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ እርምጃዎችን መቀየሳቸውንና መተግበራቸውን ያረጋግጣሉ፤

b) a money laundering or financing of terrorism investigation will be, is being or has been carried out.

2/ The provisions of sub-article (1) of this Article may not preclude disclosures or communications regarding suspicious money laundering or financing of terrorism between and among directors, officers and employees of the financial institutions and designated non-financial businesses and professions, legal counsels and appropriate competent authorities.

## 21. Action to be Taken on Reports of Suspicion

Whenever the Center has reasonable grounds to suspect money laundering or financing of terrorism, it shall forward the relevant information to the appropriate crime investigation authority, which shall decide upon further action.

## 22. Powers and Functions of Regulatory Authorities

1/ The concerned regulatory authorities shall supervise compliance by financial institutions and designated non-financial businesses and professions with the requirements set forth in this Proclamation.

2/ Without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article, the concerned regulatory authorities shall:

a) cooperate and share information with other competent authorities with respect to investigations and prosecutions relating to money laundering, predicate offences and financing of terrorism;

b) ensure that foreign branches and majority owned subsidiaries of financial institutions adopt and enforce measures consistent with this Proclamation to the extent that local laws and regulations so permit;

ሐ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይ ም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር ሊገናኙ የሚችሉ ግብይቶችን ወይም ድርጊቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በፍጥነት ለማዕከሉ ሪፖርት ያደርጋሉ፤

መ) የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች በማስፈጸም ረገድ የተወሰዱ እርምጃዎችንና የተጣሉ ቅጣቶችን በሚመለከት የስታትስቲክስ መረጃዎችን ይይዛሉ::

፫/ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ባልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች መጣሳቸውን ሲያረጋግጡ ከሚከተሉት መካከል አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን እርምጃዎችና ቅጣቶች መወሰን ይችላሉ:-

ሀ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ለ) የተወሰነ መመሪያ እንዲከበር ማዘዝ፤

ሐ) የፋይናንስ ተቋማቱና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑት የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች እየወሰዷቸው ስላሉ እርምጃዎች በየጊዜው ሪፖርት እንዲያደርጉ ማዘዝ፤

መ) ከብር ፲ሺ ባላነሰና ከብር ፩፻ሺ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ መቅጣት፤

ሠ) ግለሰቦችን በንግዱ ወይም በሙያው ዘርፍ ተቀጥረው እንዳይሠሩ መከልከል፤

ረ) ጊዜያዊ አስተዳዳሪ መመደብን ጨምሮ የሥራ አስኪያጆችን፣ የዳይሬክተሮችን እና በወሳኝነት የመቆጣጠር ሥልጣን የሚኖራቸውን ባለቤቶች ሥልጣን መገደብ፤

ሰ) ፈቃድ ማገድ ወይም መሠረዝና በሥራው ወይም በሙያው መሥራት መቀጠልን መከልከል፤ ወይም

ሸ) አግባብነት ያላቸው ሌሎች እርምጃዎች መውሰድ::

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተቋም ሥራ አስኪያጅ በከፊል ወይም በሙሉ ሥራውን እንዳያከናውን የተደረገ ክልከላ ወይም ክልከላውን ለማንሳት የተወሰደ እርምጃ በንግድ መዝገብ እንዲመዘገብ የሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን አግባብ ላለው አካል ማስተላለፍ አለበት::

c) report promptly to the Center any information concerning suspicious transactions or facts that could be related to money laundering or financing of terrorism;

d) maintain statistics concerning measures adopted and sanctions imposed in the context of enforcing this Article.

3/ The regulatory authorities may impose one or more of the following measures and sanctions where they establish violations of the obligations under this Proclamation by financial institutions and designated non-financial businesses and professions:

a) written warnings;

b) order to comply with specific instruction;

c) ordering regular reports from the financial institution and designated non-financial businesses and professions on the measures they are taking;

d) fine in an amount not less than Birr 10,000 and not greater than Birr 100,000;

e) barring individuals from employment within the business sector or profession;

f) restricting the powers of managers, directors and controlling owners, including the appointing of ad hoc administrator;

g) suspending or revoking of license and prohibiting the continuation of the business or profession; or

h) other appropriate measures.

4/ Measure that prohibits entirely or in part the manager of an institution from conducting business pursuant to sub-article (3) of this Article or any lifting of such prohibition shall be communicated by the concerned regulatory authority to the appropriate body for the purpose of registration in the commercial register.

፭/ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚወስዷቸውን እርምጃዎችና ቅጣቶች ለማዕከሉ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

## ፳፫. ሚስጥር ስለመጠበቅ

በማዕከሉ ዘንድ የሚገኝ መረጃ በተገቢውና በሕጋዊ መንገድ በእጃቸው የገባ የማዕከሉ ሃላፊዎች፣ ሠራተኞች፣ በትውስት ከሌላ ቦታ ተመድበው በማዕከሉ የሚሠሩ ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሰዎች በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በቀር መረጃውን ለሌሎች ሰዎች መግለጽ አይችሉም፡፡

## ፳፬. ከተጠያቂነት ነፃ ስለመሆን

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት በቅን ልቦና መረጃ በሚሰጡ ወይም ሪፖርት በሚያደርጉ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ላይ ወይም በዳይሬክተሮቻቸው፣ በሃላፊዎቻቸው ወይም በሠራተኞቻቸው ላይ የባንክ ሥራ ወይም የሙያ ሚስጥር ወይም የውል ግዴታ ተጥሷል በሚል የወንጀል፣ የፍትሐ ብሔር ወይም አስተዳደራዊ ክስ ሊቀርብባቸው አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፲፯ እስከ አንቀጽ ፲፱ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በቅን ልቦና ሪፖርት እስከተደረገ ድረስ ጥርጣሬ ያስከተለን ግብይት በፈጸሙ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ላይ ወይም በዳይሬክተሮቻቸው፣ በሃላፊዎቻቸው ወይም በሠራተኞቻቸው ላይ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ክስ ሊቀርብባቸው አይችልም፡፡

፫/ የ ማዕከሉ ወይም የተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሃላፊዎች፣ ሠራተኞችና በትውስት ከሌላ ቦታ ተመድበው የሚሠሩ ሠራተኞች ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ለማስፈጸም ሲባል በቅን ልቦና ለሚፈጽሙት ማናቸውም ድርጊት በፍትሐ ብሔር፣ በወንጀል ወይም በአስተዳደር ተጠያቂ አይሆኑም፡፡

5/ The regulatory authorities shall inform the Center as to the measures and sanctions imposed pursuant to sub-article (3) of this Article.

## 23. Confidentiality

The officers, employees and seconded personnel of the Center, and any other persons who obtain through legitimate and legal means information in the possession of the Center may not disclose the information, except as provided under this Proclamation.

## 24. Exemption from Liability

1/ No criminal, civil or administrative proceedings for breach of banking or professional secrecy or contract may be instituted against financial institutions and designated non-financial businesses and professions or their directors, officers or employees who in good faith submit reports or provide information in accordance with the provisions of this Proclamation.

2/ No criminal action for money laundering or financing of terrorism may be brought against financial institutions, designated non-financial businesses and professions, or their directors, officers or employees in connection with the execution of a suspicious transaction where reports of suspicions were made in good faith in accordance with the provisions from Article 17 to Article 19 of this Proclamation.

3/ Officers, employees and seconded personnel of the Center or a regulatory authority acting, in good faith, to implement this Proclamation or regulations or directives issued hereunder shall be immune from any criminal, civil or administrative liability.

## ክፍል አራት

## ስለምርመራ

### ፳፭. የምርመራ ዘዴ

፩/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የሚመለከት ማስረጃ ለማግኘት ወይም የወንጀል ፍሬን ተከታትሎ ለመለየት የዳኝነት አካላት ለተወሰነ ጊዜ:-

ሀ) በባንክ ሂሳቦችና በሌሎች ተመሳሳይ ሂሳቦች ላይ ክትትል ለማድረግ፤

ለ) የኮምፒውተር ሥርዓቶችን፣ መረቦችንና ሰርቨሮችን ለማየት፤

ሐ) መገናኛዎችን በክትትል ሥር ለማዋል ወይም ለመጥለፍ፤

መ) ድርጊቶችን፣ ባህሪዎችንና ንግግሮችን በድምጽና በምስል ለመቅረጽና ፎቶግራፍ ለማንሳት፤ እና

ሠ) የደብዳቤ ልውውጦችን ለመጥለፍና ለመያዝ፤

የሚያስችል ትዕዛዝ ለወንጀል መርማሪ አካላት መስጠት ይችላሉ::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት የምርመራ ዘዴዎች በጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረገው የተባሉት ሂሳቦች፣ የኮምፒውተር ሥርዓቶች፣ መረቦችና ሰርቨሮች፣ የስልክ መስመሮች ወይም ሰነዶች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ድርጊት የሚሳተፉ ሰዎች እየተጠቀሙባቸው ስለመሆኑ ወይም ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ የሚጠቁም አስተማማኝ ምክንያት ሲኖር ብቻ ነው::

### ፳፮. በሽፋን ሥር ስለሚደረግ ምርመራና በቁጥጥር ሥር የሚደረግ ማስተላለፍ

፩/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመመርመር ሃላፊነት የተሰጠው ሰው እነዚህን ወንጀሎች የሚመለከት ማስረጃ ለማግኘት ወይም የወንጀል ፍሬን ተከታትሎ ለመለየት ሲባል በሽፋን ሥር ከሚደረግ ምርመራና በቁጥጥር ሥር ከሚደረግ ማስተላለፍ ጋር ተያይዞ የሚፈጽመው ድርጊት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ወንጀልነት ሊፈረጅ የሚችል ቢሆንም ቅጣት አይጣልበትም::

## PART FOUR

## INVESTIGATION

### 25. Investigative Techniques

1/ For the purpose of obtaining evidence of money laundering or financing of terrorism or tracing proceeds of crime, the judicial organs may authorize crime investigation authorities, for a specific period:

a) to monitor bank accounts and other similar accounts;

b) to access computer systems, networks and servers;

c) to place under surveillance or to intercept communication;

d) to take audio or video recording or photographs of acts, behaviors and conversations; and

e) to intercept and seize correspondence.

2/ The techniques under sub-article (1) of this Article shall only be used when there are serious indications that such accounts, computer systems, networks and servers, telephone lines or documents are or may be used by persons suspected of participating in money laundering or financing of terrorism.

### 26. Undercover Operations and Controlled Delivery

1/ No punishment may be imposed on a person authorized to investigate money laundering and financing of terrorism who, for the purpose of obtaining evidence relating to these offences or the tracing of proceeds of crime, performs acts which might be construed as elements of money laundering and financing of terrorism in connection with carrying out an undercover operation or a controlled delivery.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን አሠራር ለመከተል በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል::

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በሽፋን ሥር የሚደረግ ምርመራ ወይም በቁጥጥር ሥር የሚደረግ ማስተላለፍን እንዲያስፈጽም የተመደበ ሰው ተጠርጣሪው ማንኛውንም ወንጀል እንዲፈጽም መገፋፋት የለበትም::

**፳፯. የምስክሮች ጥበቃና እንዳይታወቅ የተደረገ ምስክር ቃል**

፩/ ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት ወይም በምስክሩ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ ላይ ተመሥርቶ ምስክሩ ወይም የቤተሰቡ አባል በምስክርነቱ ምክንያት ለአደጋ የሚጋለጥ መሆኑን ሲረዳ የምስክሩ ማንነት በሚስጥር እንዲያዝ ሊወስን ይችላል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የምስክር ማንነት በሚስጥር ተይዞ የፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥል የሚደረገው ሌሎች የምርመራ ዘዴዎችን መጠቀም እውነቱ ላይ ለመድረስ በቂ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ብቻ ነው::

**፳፰. ሚስጥር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታን ወይም ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም ስለመከልከሉ**

በዚህ አዋጅ መሠረት መረጃ የመስጠት ወይም ተያያዥነት ያለው ሰነድ የማቅረብ ግዴታን ላለመወጣት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯(፪) በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሚስጥር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታን ወይም ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም አይቻልም::

## ክፍል አምስት
## የወንጀል ጥፋቶችና ቅጣቶች

**፳፱. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ**

፩/ ማንኛውም ሰው ንብረቱ የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው:-

ሀ) የንብረቱን ሕገወጥ ምንጭ ለመደበቅ ወይም ለመሸፈን ወይም አመንጪውን ወንጀል የፈጸመው ሰው ከሕግ ተጠያቂነት እንዲያመልጥ ለማድረግ ንብረቱን የለወጠ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፤

2/ The authorization of the court shall be obtained prior to any operation referred to in sub-article (1) of this Article.

3/ The person authorized to execute undercover operation or a controlled delivery pursuant to this Article may not induce the suspect to commit any offence.

**27. Witness Protection and Anonymous Testimony**

1/ If the Court, at its own initiative or at the request of a witness or the public prosecutor, concludes that the witness or a member of his family could be endangered by reason of the testimony, it may determine that the witness's identity shall be kept secret.

2/ The proceeding shall continue while the witness's identity is kept secret pursuant to sub-article (1) of this Article only if other investigative methods appear inadequate to uncover the truth.

**28. Prohibition on Invoking Professional Secrecy or Privilege**

Professional secrecy or privilege may not be invoked as a ground not to comply with the obligations under this Proclamation when the information is requested, or the production of a related document is ordered in accordance with this Proclamation, except in the cases specified in Article 17(2) of this Proclamation.

## PART FIVE
## CRIMINAL OFFENCES AND PENALTIES

**29. Money Laundering**

1/ Any person who knows or should have known that a property is the proceeds of a crime and who:

a) converts or transfers the property for the purpose of concealing or disguising the illicit origin of the property or of assisting any person who is involved in the commission of the predicate offence to evade the legal consequences of his actions;

ለ) ንብረቱን፣ የንብረቱን ትክክለኛነት፣ ምንጩን፣ ቦታውን፣ ዝውውሩን ወይም የባለቤትነት መብቱን የደበቀ ወይም እንዳይታወቅ ያደረገ እንደሆነ፤

ሐ) ንብረቱን የተረከበ፣ በይዞታው ያደረገ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ፤ ወይም

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) የተጠቀሱትን ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ተግባራትን በመፈፀም የተሳተፈ፣ ለመፈጸም ያደመ፣ የሞከረ፣ የረዳ፣ ያመቻቸ ወይም እንዲፈፀም ያማከረ እንደሆነ፤

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የንብረቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ መሠረት መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ፲ ዓመት እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ፩፻ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚጣል ቅጣት በሚከተሉት ምክንያቶች በመክበድ ከ፲፭ ዓመት እስከ ፳፭ ዓመት ጽኑ እስራት እና እስከ ብር ፩፻፶ሺ መቀጮ ሊደርስ ይችላል፦

ሀ) የተፈፀመው አመንጪ ወንጀል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው በላይ የእሥራት ቅጣት የሚያስከትል ከሆነ፤

ለ) ወንጀሉ የተፈፀመው በንግድ ወይም በሥራ ተግባርነት ተይዞ ከሆነ፤

ሐ) የተደራጀ የወንጀል ቡድን ከዓላማዎቹ አንዱ አድርጎት የፈጸመው ከሆነ፤

መ) ሕጋዊ እንዲመስል ተደርጎ የቀረበው በወንጀል ድርጊት የተገኘው ገንዘብ ወይም ንብረት ግምት ከብር ፲ሚሊዮን የሚበልጥ ከሆነ፤

ሠ) ወንጀሉ የተፈፀመው ትርፍን ለማግኘት ታስቦ ከሆነ፤ ወይም

ረ) ወንጀሉ የተፈፀመው ሌላ ወንጀል እንዲሠራ ለማመቻቸት ከሆነ።

b) conceals or disguises the true nature, source, location, disposition, movement or ownership of or rights with respect to the property;

c) acquires, possesses or uses the property; or

d) participates in the commission, conspires to commit, attempts to commit or aids, abets, facilitates or counsels the commission of any of the elements of the offence mentioned in paragraphs (a) to (c) of this sub-article;

commits an offence and shall, without prejudice to the confiscation of the property pursuant to Article 35 of this Proclamation, be punishable with rigorous imprisonment from 10 to 15 years and with fine not exceeding Birr 100,000.

2/ The penalties imposed under sub-article (1) of this Article may be increased to rigorous imprisonment from 15 to 25 years and with fine not exceeding Birr 150,000:

a) if the predicate offence carries a penalty of imprisonment exceeding that specified in sub-article (1) of this Article;

b) if the offence is perpetrated in the pursuit of a trade or occupation;

c) if the offence is perpetrated as part of the activities of an organized criminal group;

d) if the amount of fund or property laundered is more than Birr 10,000,000;

e) if the purpose is to make profit; or

f) if the purpose is promoting the carrying on of further criminal activity.

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ አፈፃፀም ሲባል፡-

ሀ) የተከሳሽ የሀሳብ ክፍል ወይም ወንጀሉን ለመፈጸም የተነሳበት ዓላማ ከተጨባጭ የሁኔታዎች ክስተት በመነሳት ግምት የሚወሰድበት ይሆናል፤

ለ) የንብረቱ ምንጭ ሕገወጥ መሆኑን ለማስረዳት በተከሳሽ ላይ በአመንጪው ወንጀል የጥፋተኛነት ፍርድ መሰጠቱ የግድ የሚያስፈልግ አይሆንም፤

ሐ) የአመንጪው ወንጀል ድርጊት ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ የተፈጸመ ቢሆንም ድርጊቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢፈፀም ኖሮ ወንጀል ሆኖ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ የመነሻው ወንጀል ይህንኑ ድርጊት ጭምር የሚያካትት ይሆናል፤

መ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል ተጠያቂነት አመንጪውን ወንጀል የፈፀመውን ሰውም የሚመለከት ይሆናል፤

ሠ) በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል ለመፈጸም መሞከር፣ መደገፍ፣ ማመቻቸት ወይም ማማከር ወንጀሉ እንደተፈጸመ ተቆጥሮ የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

**፴. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ተቀጽላ ወንጀሎች**

፩/ ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት፡-

ሀ) ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተጠይቆ የያዘውን ጥሬ ገንዘብ ወይም ለአምጪው የሚከፈሉ የገንዘብ ሰነዶች ያልገለጸ እንደሆነ፤

ለ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፬ ድንጋጌ በመተላለፍ፡-

(፩) በተመዘገበበት የውጭ አገር በአካል ከማይገኝና የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ውስጥ ከማይካተት ባንክ ጋር፤ ወይም

3/ In applying the provisions of sub-article (1) of this Article:

a) knowledge, intent, or purpose as constituent elements of the offence may be inferred from objective factual circumstances;

b) it may not be required to obtain the conviction of the predicate offence to prove the illicit origin of the property;

c) the predicate offence also includes actions committed outside of the national territory if they would have constituted offences if they had been committed within the territory of Ethiopia;

d) the offence of money laundering shall also apply to persons who have committed the predicate offence;

e) attempting, aiding, abetting, facilitating or counseling the commission of money laundering shall be punishable as if the offence had been completed.

**30. Ancillary Money Laundering Offences**

1/ Any person who intentionally or by gross negligence:

a) fails to declare currency or bearer negotiable instruments upon request by the Ethiopian Revenue and Customs Authority, when entering or leaving Ethiopia;

b) in violation of Article 4 of this Proclamation, enters into or continues business relations with:

(1) banks registered in jurisdictions where they are not physically present and are not affiliated with a regulated financial group subject to effective consolidated supervision; or

(፪) ሒሳቦቹን በተመዘገበበት የውጭ አገር በአካል የማይገኙና የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ውስጥ የማይካተት ባንክ እንዲጠቀምባቸው ከሚፈቅድ የፋይናንስ ተቋም ጋር፤

የንግድ ግንኙነት ከመሠረተ ወይም የነበረውን የንግድ ግንኙነት ካስቀጠለ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ በተደነገገው መሠረት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸውን አካላት ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለቤቶቻቸውንና የአመራር መዋቅራቸውን የሚመለከት የተሟሉ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎች ያልያዘ እንደሆነ፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮፣ አንቀጽ ፯ እና አንቀጽ ፰ መሠረት የደንበኞችን ማንነት የማጣራትና የስጋት መቀነሻ እርምጃዎችን ያልወሰደ እንደሆነ፤

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት የክትትል እርምጃዎችን ያልወሰደ እንደሆነ፤

ረ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ መሠረት መዝገብ ያልያዘ ወይም መዝገቡ እንዲወድም ወይም እንዲወገድ ያደረገ እንደሆነ፤

ሰ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ በተደነገገው መሠረት የውስጥ ቁጥጥር ፕሮግራም ተግባራዊ ያላደረገ እንደሆነ፤

ሸ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭፣ አንቀጽ ፲ ወይም አንቀጽ ፲፭ መሠረት አግባብ ባላቸው ባለሥልጣኖች ሲጠየቅ በወቅቱ መረጃ ያልሰጠ ወይም መዝገብ ያላሳየ እንደሆነ፤

ቀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ጥርጣሬዎችን በሚመለከት ለማዕከሉ ሪፖርት ያላቀረበ እንደሆነ፤

በ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ግብይቶችን በሚመለከት ለማዕከሉ ሪፖርት ያላቀረበ እንደሆነ፤

ተ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ መሠረት ሲጠየቅ ግብይት ከመፈጸም ለመቆጠብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

(2) respondent financial institutions in a foreign country if they permit their accounts to be used by banks registered in countries where they are not physically present and are not affiliated with a regulated financial group subject to effective consolidated supervision;

c) fails to maintain adequate, accurate and current information on the beneficial ownership and control structure of legal persons as required pursuant to Article 5 of this Proclamation;

d) fails to undertake the identification of customers and risk management measures as required pursuant to Article 6, Article 7 and Article 8 of this Proclamation;

e) fails to undertake the monitoring measures as required pursuant to Article 9 of this Proclamation;

f) fails to maintain the records as required pursuant to Article 10 of this Proclamation, or destroys or removes such records;

g) fails to implement internal control programs as required pursuant to Article 11 of this Proclamation;

h) fails to provide or fails to provide access to information or records in a timely fashion when so requested by the competent authorities pursuant to Article 5, Article 10 or Article 15 of this Proclamation;

i) fails to submit a report relating to a suspicion to the Center as required pursuant to Article 17 of this Proclamation;

j) fails to submit a report relating to a cash transaction to the Center as required pursuant to Article 18 of this Proclamation;

k) does not refrain from carrying out a transaction when so required pursuant to Article 19 of this Proclamation; or

ቸ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ የተደነገገውን በመተላለፍ መረጃ ለደንበኛ ወይም ለሌላ ሦስተኛ ሰው አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከብር ፭ሺ እስከ ብር ፲ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው ማንኛውም ተቀጽላ ወንጀል ጥፋተኛ የሆነ ሰው ከእሥራቱና የገንዘብ ቅጣቱ በተጨማሪ ወንጀሉን ለመፈጸም እድል የፈጠረለትን የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ለዘለቄታው ወይም ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዳይሠራ ሊታገድ ይችላል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚጣሉ ቅጣቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሠረት ሊወስዱ የሚ ችሏቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች አያስቀሩም::

**፴፩. ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት**

፩/ ማንኛውም ሰው:-

ሀ) ገንዘቡ በሙሉ ወይም በከፊል:-

(፩) የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም፣

(፪) ለአሸባሪ መጠቀሚያ፣ ወይም

(፫) ለሽብርተኛ ድርጅት መጠቀሚያ፣

እንዲውል በማሰብ ወይም እንደሚውል እያወቀ በማንኛውም መንገድ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገዛ ፈቃዱ ገንዘብ የሰጠ ወይም የሰበሰበ ወይም ገንዘብ ለመስጠትም ሆነ ለመሰብሰብ የሞከረ እንደሆነ፣

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ወንጀል በመፈጸም በአባሪነት የተሳተፈ እንደሆነ፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ወንጀል ለማስፈጸም ሌሎችን ያደራጀ ወይም አመራር የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም

l) discloses information to a customer or a third party in contravention of Article 23 of this Proclamation;

commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from three to five years and fine from Birr 5,000 to Birr 10,000.

2/ A person found guilty of an ancillary offence set forth in sub-article (1) of this Article may, in addition to the imprisonment and fine, be banned permanently or for a maximum period of five years from pursuing the business or profession which provided the opportunity for the offence to be committed.

3/ Penalties imposed for ancillary offences in accordance with sub-article (1) of this Article do not exclude the administrative measures that are available to the regulatory authorities pursuant to Article 22 of this Proclamation.

**31. Financing of Terrorism**

1/ Any person who:

a) by any means, directly or indirectly, willfully, provides or collects funds, or attempts to do so, with the intention that they should be used or with the knowledge that they are to be used in full or in part:

(1) to carry out a terrorist act; or

(2) by a terrorist; or

(3) by a terrorist organization;

b) participates as an accomplice in an offence within the meaning of paragraph (a) of this sub-article;

c) organizes or directs others to commit an offence within the meaning of paragraph (a) of this sub-article; or

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) የተመለከቱትን ወንጀሎች የሚያቋቁሙ ተግባራትን በመፈፀም የተሳተፈ፣ ለመፈፀም ያደመ፣ የሞከረ፣ የደገፈ፣ ያመቻቸ ወይም እንዲፈፀም ያማከረ እንደሆነ፣

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ መሠረት የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ፲ ዓመት እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ፩፻ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚጣል ቅጣት በሚከተሉት ምክንያቶች በመክበድ ከ፲፭ ዓመት እስከ ፳፭ ዓመት ጽኑ እስራት እና እስከ ብር ፩፻፶ሺ መቀጮ ሊደርስ ይችላል:-

ሀ) ወንጀሉ የተፈፀመው በንግድ ወይም በሥራ ተግባርነት ተይዞ ከሆነ፤ ወይም

ለ) የተደራጀ የወንጀል ቡድን ከዓላማዎቹ አንዱ አድርጎት የፈጸመው ከሆነ::

፫/ ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ወንጀል መሳተፍ፣ ወንጀሉን ለመፈጸም ማደም፣ መሞከር፣ መደገፍ፣ ማመቻቸት ወይም ማማከር ወንጀሉ እንደተፈጸመ ተቆጥሮ የሚያስቀጣ ይሆናል::

**፴፪. ሌሎች ወንጀሎች**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠን ገንዘብ ወይም ንብረት የማገድ፣ የመያዝ ወይም የመውረስ ትዕዛዝ ያላከበረ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ፭ሺ እስከ ብር ፲ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል::

፪/ ለዚህ አዋጅ ዓላማ:-

ሀ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ወይም በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ከተሰጠ ትዕዛዝ ጋር በተያያዘ ለሚደረግ ምርመራ ጠቃሚ የሆነ ሰነድ ወይም ማቴሪያል ወደ ሐሰት የለወጠ፣ ያጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ያስወገደ ወይም ወደ ሐሰት ሰነድነት እንዲለወጥ፣ እንዲጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ እንዲወገድ የፈቀደ እንደሆነ፤

d) participates in the commission, conspires to commit, attempts to commit or aids, abets, facilitates or counsels the commission of any of the elements of the offence referred to from paragraph (a) to (c) of this sub-article;

commits an offence and shall, without prejudice to the confiscation of the funds pursuant to Article 35 of this Proclamation, be punishable with rigorous imprisonment from 10 to 15 years and with fine not exceeding Birr 100,000.

2/ The penalties imposed under sub-article (1) of this Article may be increased to rigorous imprisonment from 15 to 25 years and with fine not exceeding Birr 150,000:

a) if the offence is perpetrated in the pursuit of a trade or occupation; or

b) if the offence is perpetrated as part of the activities of an organized criminal group.

3/ Participating, conspiring, attempting, aiding, abetting, facilitating or counseling the commission of financing of terrorism shall be punishable as if the offence had been completed.

**32. Other Offences**

1/ Any person who fails to comply with orders of freezing, seizing or confiscation of funds or property pursuant to the provisions of this Proclamation commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from three to five years and fine from Birr 5,000 to Birr 10,000.

2/ For the purpose of this Proclamation any person who:

a) falsifies, conceals, destroys or otherwise disposes of or causes or allows the falsification, concealment, destruction or disposal of any document or material which is or is likely to be relevant to an investigation of money laundering or financing of terrorism or in relation to any order made in accordance with the provisions of this Proclamation;

ለ) በማዕከሉ ዘንድ የተቀመጠውን መረጃ ሆነ ብሎ ያጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ለሚፈለገው ዓላማ እንዳይውል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ድርጊት ላይ ምስክር የሆነን ወይም ለመሆን የሚችል ሰውን እንዳይመሰክር የደለለ ወይም ያስፈራራ ወይም በምስክሩ ወይም ከምስክሩ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ የሀይል ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፤

ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ፲ሺ እስከ ብር ፶ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፴፫. **በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ የሚጣል ቅጣት**

፩/ የመንግሥት አካል ያልሆነ ማንኛውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፡-

ሀ) ወክሎት በሚሠራ ወይም በዚሁ አካል ውስጥ የመቆጣጠር ሥልጣን ያለው ግለሰብ በተናጠልም ሆነ ከሚመራው ቡድን ጋር በመሆን ሲሠራ አካሉን በመወከል ወይም ለአካሉ ጥቅም ሲባል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) በአካሉ ሃላፊነት ሥር የሚሠራን ግለሰብ በሚመለከት ሊደረግ በሚገባው ክትትልና ቁጥጥር መጓደል ምክንያት አካሉን በመወከል ወይም ለአካሉ ጥቅም ሲባል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ፤

ግለሰቦቹ በወንጀል ፈጻሚነት ወይም አባሪነት የጥፋተኝነት ፍርድ ቢሰጥባቸውም ባይሰጥባቸ ውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ ወይም አንቀጽ ፴፩ የተመለከተው የገንዘብ ቅጣት በአሥር ተባዝቶ ይፈጸምበታል፡፡

b) intentionally destroys or in any other way tampers with information kept by the Center; or

c) induces or threatens a person who is or can be a witness for an act of money laundering or financing of terrorism or uses violence against the witness or a person who has close relationship with the witness to prevent the witness from testifying;

shall be punishable with rigorous imprisonment from five to ten years and fine from Birr 10,000 to Birr 50,000.

33. **Penalties Applicable to Legal Persons**

1/ Any legal person other than government organs:

a) on whose behalf or for whose benefit money laundering or financing of terrorism has been committed by any natural person, acting either individually or as part of a team, who has a leading position within it, based on a power of representation of the legal person or an authority to exercise control within the legal person; or

b) where lack of supervision of or control over a natural person acting under its authority has made possible the commission of money laundering or financing of terrorism on its behalf or for its benefit;

shall, irrespective of the conviction of those individuals as perpetrators or accomplices to the offence, be punished by a fine of an amount equal to ten times the fine specified for natural persons under Article 29 or Article 31 of this Proclamation.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በወንጀል ተጠያቂ የተደረገ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፣ በፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ውሳኔ:-

ሀ) የተወሰኑ የንግድ ሥራዎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዘለቄታው ወይም ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዳያካሂድ ሊታገድ፤

ለ) ወንጀሉን ለመፈጸም በጥቅም ላይ የዋለውን የሥራ ቦታውን ለዘለቄታው ወይም ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲዘጋ፤ ወይም

ሐ) እንዲፈርስና ሂሳቡ እንዲጣራ ሊደረግ፤

ይችላል::

፫/ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ መሠረት በወንጀል መጠየቁ ወንጀሉን በመፈጸም የተሳተፉ ግለሰቦችን ከተጠያቂነት አያድናቸውም::

## ፴፬. የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች

የወንጀሉ ፈጻሚ ለፍትሕ አካላት:-

፩/ ወንጀሉ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመከላከል ወይም ለመቀነስ፤

፪/ የወንጀሉን ሌሎች ፈጻሚዎች ለመለየት ወይም ለፍርድ ለማቅረብ፤

፫/ ከወንጀሉ ጋር የተያያዘ ማስረጃ ለማግኘት፤ ወይም

፬/ የተደራጁ የወንጀለኛ ቡድኖችን ሀብታቸውን ወይም በወንጀል ፍሬነት ያገኙትን ለማሳጣት፤

የሚያስችላቸውንና በሌላ መንገድ ሊያገኙ የማይችሉትን መረጃ የሰጣቸው እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ ወይም አንቀጽ ፴፩ የተመለከቱት ቅጣቶች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፩፻፸፱ የተመለከቱት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ሊቀነሱለት ይችላሉ::

## ፴፭. ስለመውረስ

፩/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም በአመንጪው ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠ እንደሆነ:-

ሀ) የወንጀሉ ፍሬ የሆነው ገንዘብ ወይም ንብረት፣ ተቀላቅሎት ወይም ተለውጦበት የተገኘ ንብረትን ጨምሮ፤

2/ The legal person made criminally liable under sub-article (1) of this Article may, by the additional judgment of the court, be:

a) barred permanently or for a maximum period of five years from directly or indirectly carrying on certain business activities;

b) ordered to close permanently or for a maximum period of five years its premises which were used for the commission of the offence; or

c) wound up.

3/ The criminal liability of a legal person under this Article may not preclude the individual liabilities of the natural persons involved in the commission of the crime.

## 34. Mitigating Circumstances

The penalties provided for in Article 29 or Article 31 of this Proclamation may be reduced, within the limits allowed by Article 179 of the Criminal Code, if the perpetrator of the offence provides the justice organs with information they would not have otherwise obtained so as to assist them in:

1/ preventing or limiting the effects of the offence;

2/ identifying or prosecuting other perpetrators of the offence;

3/ obtaining evidence relating to the offence; or

4/ depriving organized criminal groups of their resources or the proceeds of crime.

## 35. Confiscation

1/ In the event of a conviction for money laundering or a predicate offence, or financing of terrorism, an order shall be issued by the court for the confiscation of:

a) funds or property constituting the proceeds of crime, including property intermingled with or exchanged for such proceeds;

ለ) ከወንጀሉ ፍሬ የተገኘን ገቢና ሌሎች ጥቅሞች የሚመለከት ገንዘብ ወይም ንብረት፤

ሐ) ለወንጀሉ መፈጸሚያነት የዋለ ንብረት፤

መ) ባለቤትነቱ የተላለፈለት ምንጩ ሕገወጥ መሆኑን ሳያውቅና ተገቢ የሆነ ዋጋ ከፍሎበት ወይም ለሰጠው ተመጣጣኝ አገልግሎት ታስቦለት ወይም በሌላ ሕጋዊ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካላመነ በስተቀር በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (ሐ) ከተመለከቱት መካከል ለማንኛውም ወገን የተላለፈ ገንዘብ ወይም ንብረት፤ ወይም

ሠ) ከወንጀሉ ፍሬ ጋር ተመጣጣኝ ግምት ያለው የወንጀል ፈጻሚው ንብረት፤

እንዲወረስ ፍርድ ቤቱ ያዛል።

፪/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም በአመንጪው ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ወንጀል የተፈረደበት ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የያዘውና በወንጀሉ ከመከሰሱ አስቀድሞ ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ጥፋተኛ የተሰኘበት ወንጀል ውጤት ነው ብሎ ለመገመት የሚያስችል በቂ ምክንያት ካለና ግለሰቡ በሕጋዊ መንገድ ያፈራው ስለመሆኑ በማስረጃ ማረጋገጥ ካልቻለ በተጨማሪነት እንዲወረስ ፍርድ ቤቱ ሊወስን ይችላል።

፫/ የወንጀሉ ፈጻሚ ባለመታወቁ፣ በመሰወሩ ወይም በመሞቱ ምክንያት የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠት ባይቻልም፣ ፍርድ ቤቱ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም የአመንጪው ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል መፈጸሙን ካረጋገጠና የተያዘው ንብረት የወንጀል ፍሬ ወይም የወንጀል መፈጸሚያ መሆኑን የሚያሳይ በቂ ማስረጃ ከቀረበለት እንዲወረስ ሊወስን ይችላል።

፬/ የመውረሻ ትዕዛዝ የሚወረሰውን ንብረት መግለጽና ንብረቱን ለመለየትና የሚገኝበትን ሥፍራ ለማመልከት የሚያስፈልጉ ዝርዝሮችን መያዝ አለበት።

b) funds or property constituting income and other benefits obtained from the proceeds of crime;

c) the instrumentalities;

d) funds or property referred to from paragraph (a) to (c) of this sub-article that has been transferred to any party, unless the court finds that the owner of such property acquired them by paying a fair price or in return for the provision of services corresponding to their value or on any other legitimate grounds, and that he was unaware of its illicit origin; or

e) property of the perpetrator of the offence the value of which corresponds to that of the proceeds of crime.

2/ The court may also order confiscation of funds or property belonging to directly or indirectly to a person convicted of money laundering or a predicate offence or financing of terrorism, which were acquired during a period of five years prior to being charged with the offence, if there are reasonable grounds indicating that such funds or property are the result of the offence of which the person was convicted, and the person failed to prove that the property was obtained legally.

3/ If, in case where an offence involving money laundering or a predicate offence, or financing of terrorism, is established by the court and the perpetrator thereof cannot be convicted because he is unknown, he absconded or died, the court may nevertheless order the confiscation of the seized funds or property if sufficient evidence is adduced that it constitutes proceeds of crime or instrumentalities.

4/ The confiscation order shall specify the property concerned and contain the necessary details to identify and locate it.

፭/ ፍርድ ቤቱ ዓላማው የንብረቱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መወረስ ለማስቀረት የሆነን ማንኛውንም ህጋዊ ሰነድ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ማድረግ ይችላል፤ ሆኖም ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገው ውል የተፈረመው ዋጋ በተከፈለበት ግንኙነት ላይ ተመሥርቶ ከሆነ በቅን ልቦና ክፍያ የፈጸመው ተዋዋይ ወገን የከፈለው ገንዘብ ብቻ ተመላሽ ይደረግለታል::

**፴፮. ማገድና መያዝ**

፩/ ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ህግ አመልካችነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ መሠረት ሊወረስ የሚችል የወንጀል ፍሬ ወይም የወንጀል መፈጸሚያ ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያስችሉ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጊዜያዊ እርምጃዎችን ጨምሮ የማገድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚደረገው በቅን ልቦና የተገኙ የሦስተኛ ወገን መብቶች ሳይነኩ ነው::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተወሰነን ማንኛውም ጊዜያዊ እርምጃ ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ህግ፣ በወንጀሉ ተጠርጣሪ ወይም በንብረቱ ላይ መብት አለኝ በሚል ሰው አመልካችነት በማናቸውም ጊዜ ሊያነሳው ይችላል::

**፴፯. ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዘ ገንዘብን ስለማገድ**

፩/ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ምዕራፍ ሰባት መሠረት የሰየማቸው አሸባሪዎች፣ አሸባሪዎችን በገንዘብ የሚረዱ እና ሽብርተኛ ድርጅቶች ገንዘብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ይታገዳል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጠው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ እግዱ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎችና ሁኔታዎች እና ጸንቶ የሚቆይበትን የጊዜ ገደብ የሚገልጽ ሆኖ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ታትሞ መውጣት አለበት::

5/ The court may invalidate any legal instrument, the purpose of which is to avoid the confiscation of the property pursuant to sub-article (1) of this Article; provided, however, that if the invalidated legal instrument is entered into for value the acquiring party acting in good faith shall be reimbursed only for the amount actually paid.

**36. Freezing and Seizing**

1/ The court may, either at its own initiatives or at the request of the public prosecutor, issue order of freezing or seizing, including other appropriate provisional measures, intended to preserve availability of funds or property and instrumentalities that may be subject to confiscation in accordance with Article 35 of this Proclamation.

2/ The provision of sub-article (1) of this Article shall apply without prejudice to the rights of third parties acquired in good faith.

3/ Any provisional measure imposed pursuant to sub-article (1) of this Article may be lifted at any time by the court that ordered the measure on its own initiative or at the request of the public prosecutor, the suspect or person claiming rights to the property.

**37. Freezing of Funds Associated with Financing of Terrorism**

1/ The funds of terrorists, those who finance terrorism and terrorist organizations, designated by the United Nations Security Council acting pursuant to Chapter VII of the United Nations Charter, shall be frozen by the decision of the Council of Ministers.

2/ The decision of the Council of Ministers to be issued pursuant to sub-article (1) of this Article shall define the terms, conditions and time limits applicable to the freezing, and shall be published in newspapers having wide circulation.

፫/ የ ሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡-

ሀ) በእጃቸው የሚገኘውንና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሱት ግለሰቦችና አካላት ጋር ግንኙነት ያለውን ገንዘብ ወዲያውኑ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ፤ እና

ለ) የተባለው ገንዘብ በእጃቸው መኖሩን ሳይዘገዩ ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ፤

አለባቸው፡፡

## ክፍል ስድስት

## ዓለም አቀፍ ትብብር

### ፴፰. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፯(፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያላቸው ባለሥልጣኖች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን በሚመለከት ወንጀለኛን አሳልፎ በመስጠት፣ በመመርመርና ለፍርድ በማቅረብ ረገድ ከሌሎች አገሮች አግባብ ያላቸው ባለሥልጣኖች ጋር በሚቻለው መጠን ሁሉ የጋራ የህግ ድጋፍ ትብብር ማድረግ አለባቸው፡፡

፪/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ዓላማ እንደ ፖለቲካ ወንጀል፣ ከፖለቲካ ወንጀል ጋር ግንኙነት እንዳለው ወንጀል ወይም በፖለቲካ ፍላጎት በመገፋፋት እንደተፈጸመ ወንጀል አይቆጠርም፡፡

### ፴፱. የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ

፩/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በሚመለከት የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ በሌላ አገር አመልካችነት ሲቀርብ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ይስተናገዳል፡፡

፪/ የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ በተለይ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

ሀ) ከሰዎች ማስረጃ ወይም ቃል መቀበልን፤

3/ Following the decision of the Council of Ministers, the financial institutions and designated non-financial businesses and professions shall:

a) immediately freeze those funds they are holding and linked with the persons and entities referred to in sub-article (1) of this Article; and

b) report without delay to the Center the existence of such funds.

## PART SIX

## INTERNATIONAL COOPERATION

### 38. General Provisions

1/ Without prejudice to the provisions of Article 47(1) of this Proclamation, the competent authorities shall provide the widest possible range of cooperation to the competent authorities of other states for purposes of mutual legal assistance in connection with extradition and criminal investigations and proceedings related to money laundering and financing of terrorism.

2/ For the purposes of this Proclamation, money laundering and financing of terrorism may not be regarded as political offences, or offences connected with a political offence, or offences inspired by political motives.

### 39. Requests for Mutual Legal Assistance

1/ Upon application by a foreign state, requests for mutual legal assistance in connection with money laundering or financing of terrorism shall be executed in accordance with the provisions of this Part.

2/ Mutual legal assistance may include in particular:

a) taking evidence or statements from persons;

ለ) የተያዙ ሰዎችን ወይም ፈቃደኛ የሆኑ ምስክሮችን ማስረጃ እንዲሰጡ ወይም ምርመራውን እንዲረዱ ለጠያቂው አገር የዳኝነት አካላት ማቅረብን፤

ሐ) የፍርድ ቤት ሰነዶችን ለሚመለከታቸው እንዲደርሱ ማድረግን፤

መ) የፍተሻና የመያዝ ትዕዛዞች ማስፈጸምን፤

ሠ) ቁሳቁሶችንና ሥፍራዎችን መፈተሽን፤

ረ) መረጃዎችን፣ የማስረጃ ቁሳቁሶችንና የባለሙያ ግምቶችን መስጠትን፤

ሰ) የመንግሥት፣ የባንክ፣ የፋይናንስ፣ የተቋም ወይም የንግድ ሥራ መዝገቦችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶችና መዝገቦች ዋና ወይም የተረጋገጡ ቅጅዎችን መስጠትን፤

ሸ) የወንጀል ፍሬን፣ የወንጀል መፈጸሚያዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ለማስረጃነት ወይም ለመውረስ ዓላማ ተከታትሎ መለየትን ወይም ማግኘትን፤

ቀ) ገንዘብን ወይም ንብረትን መውረስን፤

በ) የማገድ ወይም የመያዝ እና ሌሎች ጊዜያዊ እርምጃዎችን ማስፈጸምን፤

ተ) ሌሎች ከኢትዮጵያ ሕጎች ጋር የማይቃረኑ የጋራ ትብብር የህግ ድጋፍ ጥያቄዎችን።

b) assisting in making detained persons or voluntary witnesses available to the judicial authorities of the requesting state in order to give evidence or assist in investigations;

c) effecting service of judicial documents;

d) executing searches and seizures;

e) examining objects and sites;

f) providing information, evidentiary items and expert evaluations;

g) providing originals or certified copies of relevant documents and records, including government, bank, financial, corporate or business records;

h) identifying or tracing the proceeds of crime or instrumentalities or other things for evidentiary or confiscation purposes;

i) confiscation of funds or property;

j) executing freezing or seizure and other provisional measures;

k) any other form of mutual legal assistance not contrary to the laws of Ethiopia.

## ፵. ድጋፍ ስለመከልከል

፩/ የጋራ ትብብር የህግ ድጋፍ ጥያቄ ተቀባይነት ሊነፈገው የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ይሆናል:-

ሀ) በጠያቂው አገር ሕግ መሠረት አግባብ ባለው አካል የቀረበ ጥያቄ ካልሆነ ወይም ይዘቱ በመሠረታዊ ደረጃ ከዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፰ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣም ካልሆነ፤

ለ) አፈጻጸሙ የኢትዮጵያን ሕግና ሥርዓት፣ ሉዓላዊነት፣ ደህንነት፣ የሕዝብ ጥቅም ወይም ሌሎች መሠረታዊ ጥቅሞችን የሚነካ ከሆነ፤

ሐ) ጥያቄው የሚመለከተው የወንጀል ድርጊት በኢትዮጵያ ውስጥ በመዳኘት ላይ ከሆነ ወይም የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፤

## 40. Refusal to Execute Requests

1/ A request for mutual legal assistance may be refused only if:

a) it was not made by a competent authority according to the legislation of the requesting country, or its contents are in substantial non-conformity with Article 48 of this Proclamation;

b) its execution is likely to prejudice the law and order, sovereignty, security, public interest or other essential interests of Ethiopia;

c) the offence to which it relates is the subject of criminal proceedings or has already been the subject of a final judgment in the territory of Ethiopia;

መ) እርምጃው ወይም ትዕዛዙ በተፈላጊው ግለሰብ ላይ ያነጣጠረው በግለሰቡ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ዜግነት፣ የዘር ሐረግ፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ ጾታ ወይም አቋም ላይ ብቻ ተመሥርቶ መሆኑን ለማመን የሚያስችል ተጨባጭ ምክንያት ሲኖር፤

ሠ) በድጋፍ ጥያቄው ውስጥ የተጠቀሰው ወንጀል በኢትዮጵያ ሕግ በወንጀልነት የተፈረጀ ካልሆነ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ከተደነገገው ወንጀል ጋር የሚያመሳስለው ባህሪ የሌለው ከሆነ፤

ረ) በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተጠቀሰውን ወንጀል በሚመለከት የተጠየቀውን እርምጃ ወይም ተመሳሳይ ውጤት የሚኖረውን ሌላ እርምጃ መውሰድ የማይፈቀድ ከሆነ፤

ሰ) በኢትዮጵያ ወይም በጠያቂው አገር ሕግ በተደነገገ የይርጋ ጊዜ ምክንያት የተጠየቀውን እርምጃ ማዘዝ ወይም ማስፈጸም የማይፈቀድ ከሆነ፤

ሸ) እንዲፈጸም የተጠየቀውን ውሳኔ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ተፈጻሚ ማድረግ የማይቻል ሲሆን፤ ወይም

ቀ) በውጭ አገር የተሰጠው ውሳኔ የተከሳሹን የመከላከል መብት በበቂ ደረጃ ባላስተናገደ ሁኔታ የተሰጠ ከሆነ::

፪/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የጋራ ትብብር የህግ ድጋፍ ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረበትን ምክንያት አግባብ ላለው የጠያቂው አገር ባለሥልጣን ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት::

## ፵፩. የምርመራ ሥራን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ

፩/ አግባብ ያለው የጠያቂው አገር ባለሥልጣን በኢትዮጵያ ሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ጋር የማይቃረን ለየት ያለ ሥርዓትን ተከትሎ እንዲፈጸም ካልጠየቀ በስተቀር ምርመራ የሚካሄደው በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገገውን የምርመራ ሥርዓት ተከትሎ ነው::

፪/ የጠያቂው አገር አግባብ ያለው ባለሥልጣን የመደበው የመንግሥት ሃላፊ የምርመራ ሥራውን አፈጻጸም እንዲታዘብ ሊፈቀድለት ይችላል::

d) there are substantial grounds for believing that the measure or order being sought is directed at the person in question solely on account of that person's race, religion, nationality, ethnic origin, political opinions, gender or status;

e) the offence referred to in the request is not provided for under the legislation of Ethiopia or does not have features in common with an offence provided for under the legislation of Ethiopia;

f) under the legislation of Ethiopia, the measures requested, or any other measures having similar effects, are not permitted with respect to the offence referred to in the request;

g) the measures requested cannot be ordered or executed by reason of period of limitations under the legislation of Ethiopia or the law of the requesting state;

h) the decision whose execution is being requested is not enforceable under the legislation of Ethiopia; or

i) the decision rendered abroad was issued under conditions that did not afford sufficient protections with respect to the rights of the defendant.

2/ The competent authority shall promptly inform the competent authority of the requesting state of the grounds for refusal to execute the request.

## 41. Requests for Investigative Measures

1/ Investigative measures shall be undertaken in conformity with the procedural rules of Ethiopia unless the competent foreign authority has requested a specific procedure not contrary to such rules.

2/ A public official authorized by the competent authority of the requesting state may be allowed to attend the execution of the investigative measures.

**፵፪. ጊዜያዊ እርምጃዎች መውሰድን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ**

፩/ በጠያቂው አገር እንዲወሰዱ የተጠየቁ ጊዜያዊ እርምጃዎች አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ይፈጸማሉ:: እንዲወሰዱ የተጠየቁት እርምጃዎች በጥቅል አነጋገር የተገለጹ ከሆነ በሕጉ የተደነገጉትና ይበልጥ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች ይወሰዳሉ::

፪/ የተጠየቁት እርምጃዎች በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገጉ ካልሆኑ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገጉትና በውጤት ይበልጥ ቅርበት ያላቸው እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል::

፫/ ጊ ዜያዊ እርምጃዎችን ስለማንሳት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮(፫) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፤ ሆኖም እርምጃዎቹ እንዲነሱ ከመደረጋቸው በፊት አግባብ ያለው የጠያቂው አገር ባለሥልጣን እንዲያውቀው ይደረጋል::

**፵፫. የመውረስ እርምጃን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ**

፩/ የመውረሻ ትዕዛዝ እንዲፈጸም የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በጠያቂው አገር ፍርድ ቤት ለተሰጠው ውሳኔ እውቅና ሰጥቶ ማስፈጸም ወይም በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የመውረሻ ትዕዛዝ ለማስጠት ጉዳዩን ለዐቃቤ ሕግ መምራትና ትዕዛዙ ከተሰጠም ማስፈጸም አለበት::

፪/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በጠያቂው አገር ፍርድ ቤት ለተሰጠው የመውረሻ ትዕዛዝ እውቅና ሰጥቶ የሚያስፈጽመው ከሆነ ትዕዛዙ የተመሠረተባቸውን የመረጃ ግኝቶች እንዳሉ ወስዶ ማስፈጸም ይኖርበታል::

፫/ የመውረሻ ትዕዛዙ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ ድንጋጌዎች የሚሸፈንና በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ገንዘብን ወይም ንብረትን የሚመለከት መሆን አለበት::

፬/ ከጠያቂው አገር ጋር የተደረገ የተለየ ስምምነት ካልኖረ በስተቀር የሚመለከተው የመንግሥት አካል የተወረሰውን ንብረት የማስወገድ ሥልጣን ይኖረዋል::

**42. Requests for Provisional Measures**

1/ Provisional measures requested by a state shall be undertaken in accordance with the applicable law of Ethiopia. If the request is worded in general terms, the most appropriate measures provided by law shall be used.

2/ Where the applicable law of Ethiopia does not provide for the measures requested, the competent authority may substitute those measures provided for in the law whose effects correspond most closely to the requested measures.

3/ The provisions relating to the lifting of provisional measures as laid down in Article 36(3) of this Proclamation shall be applicable; provided, however, that beforc lifting the provisional measures applied, the competent authority of the requesting state shall be informed thereof.

**43. Requests for Confiscation**

1/ In the case of a request for mutual legal assistance seeking the execution of a confiscation order, the competent authority shall either recognize and enforce the confiscation order made by a court of the requesting state or submit the request to the public prosecutor for the purpose of obtaining a confiscation order from the Ethiopian court and, if such order is granted, enforce it.

2/ Where the competent authority recognizes and enforces a confiscation order issued by the court of the requesting state, it shall be bound by the findings of fact on which the order is based.

3/ The confiscation order shall apply to the funds or property referred to in Article 35 of this Proclamation and situated in the territory of Ethiopia.

4/ The appropriate government organ shall have the power of disposal of confiscated property unless provided otherwise under an agreement concluded with the requesting state.

## ፵፬. አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ

፩/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በሚመለከት ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን በሆነችበት አግባብ ያለው ዓለም አቀፍ ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ይስተናገዳል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ መስጠት የሚቻለው ለጥያቄው መነሻ የሆነው ወንጀል ወይም ተመሳሳዩ በጠያቂው አገርና በኢትዮጵያ ሕግ በወንጀልነት የተፈረጀ ሲሆን ነው፡፡

፫/ የጠያቂው አገር ሕግ ወንጀሉን ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ወይም ባልሆነ የወንጀል ምድብ ወይም ስያሜ ቢገልጸውም ድርጊቱ በሁለቱም አገር ሕጎች በወንጀልነት የተፈረጀ እስከሆነ ድረስ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡

## ፵፭. አሳልፎ የመስጠት ጥያቄን ስለአለመቀበል

፩/ ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የሚከተሉት ምክንያቶች ሲኖሩ ተቀባይነት አይሰጠውም፡-

ሀ) ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀው ሰው የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ሲሆን፤

ለ) ጥያቄው የቀረበው ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀውን ሰው በጾታው፣ በዘሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በዜግነቱ፣ በዘር ሃረጉ ወይም በፖለቲካ አመለካከቱ ሳቢያ ለመክሰስና ለመቅጣት ተፈልጎ መሆኑን ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሲኖር፤

ሐ) አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የቀረበበትን ወንጀል በሚመለከት በኢትዮጵያ ውስጥ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን፤

መ) ከሁለቱ አገሮች በአንዳቸው ሕግ መሠረት ምህረትና የይርጋ ጊዜ ገደብን ጨምሮ ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀውን ሰው ከመክሰስ ወይም ከመቅጣት ነፃ የሚያደርግ ማንኛውም ምክንያት ሲኖር፤ ወይም

## 44. Extradition Requests

1/ An extradition request related to money laundering or financing of terrorism shall be executed in accordance with the provisions of this Part unless otherwise provided in the applicable extradition treaty to which Ethiopia is a party.

2/ Extradition based upon this Proclamation shall be carried out only if the offence giving rise to the request for extradition or a similar offence is provided for under the legislation of the requesting state and of Ethiopia.

3/ The requirements of sub-article (2) of this Article shall be deemed fulfilled irrespective of whether the laws of the requesting state places the offence within the same category of offence or denominate the offence by the same terminology as in Ethiopia, provided the conduct underlying the offence for which assistance is sought is a criminal offence under the laws of both states.

## 45. Refusal to Extradite

1/ Extradition may not be granted if:

a) the person whose extradition is requested is a national of Ethiopia;

b) there are substantial grounds to believe that the request for extradition has been made for the purpose of prosecuting and punishing a person on account of that person's sex, race, religion, nationality, ethnic origin or political opinions;

c) a final judgment has been rendered in Ethiopia in respect of the offence for which extradition is requested;

d) the person whose extradition is requested has, under the legislation of either country, become immune from prosecution or punishment for any reason, including period of limitations and amnesty; or

ሠ) ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀው ሰው የማሰቃየት ወይም የጭካኔ ድርጊት ወይም ኢሰብዓዊ ወይም የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የተፈጸመበት ወይም ሊፈጸምበት የሚችል ስለመሆኑ፣ ወይም በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን አንቀጽ ፲፬ እንደተደነገገው በወንጀል ፍርድ ሂደት መሠረታዊ መብቶቹን ተነፍጎ እንደነበር ወይም ሊነፈግ እንደሚችል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሲኖር::

፪/ ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የሚከተሉት ምክንያቶች ሲኖሩ ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል:-

ሀ) አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የቀረበበትን ወንጀል የሚመለከት ክስ በኢትዮጵያ ውስጥ በመታየት ላይ ሲሆን፤

ለ) አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የቀረበበት ወንጀል የተፈጸመው ከሁለቱም አገሮች የግዛት ክልል ውጪ ሲሆን፤

ሐ) ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀው ሰው በፈጸመውና ለጥያቄው መነሻ በሆነው ድርጊት ምክንያት በጠያቂው አገር ውስጥ ባለ መደበኛ ባልሆነ ወይም ፍትሃዊነት በሌለው ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት አካል ተፈርዶበት የነበረ ወይም ተከሶ ሊፈረድበት የሚችል ሲሆን፤

መ) የወንጀሉ ሁኔታና የጠያቂው አገር ጥቅሞች ጭምር ተገናዝበው ቢታዩም ተላልፎ እንዲሰጥ ከተጠየቀው ሰው የእድሜ፣ የጤና ወይም ሌሎች የግል ሁኔታዎች አንፃር ሲታይ አሳልፎ መስጠቱ ከሰብዓዊነት መመዘኛዎች ጋር የማይጣጣም ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም

ሠ) ጥያቄው ተከሳሹ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ስለክሱ በቂ መረጃ ሳይኖረው ወይም ራሱን ለመከላከል በቂ የመዘጋጃ ዕድል ሳይኖረው በሌለበት በተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ላይ ተመሥርቶ የቀረበ ከሆነና ክሱ እንደገና ባለበት እንዲታይ እድል ያላገኘ ወይም ሊያገኝ የማይችል ሲሆን::

e) there are substantial grounds to conclude the person whose extradition is requested has been or would be subjected to torture or cruel, inhuman or degrading treatment or punishment or if that person has not received or would not receive the minimum guarantees in criminal proceedings, as provided under Article 14 of the International Covenant on Civil and Political Rights.

2/ Extradition may be refused if:

a) a prosecution in respect of the offence for which extradition is requested is pending in Ethiopia;

b) the offence for which extradition is requested has been committed outside the territory of both countries;

c) the person whose extradition is requested has been sentenced for the conduct which gives rise to the request or would be liable to be tried and sentenced in the requesting state by an irregular or fundamentally unfair extraordinary or ad hoc court or tribunal;

d) while also taking into account the nature of the offence and the interests of the requesting state, it is considered that the extradition of the person in question would be incompatible with humanitarian considerations in view of the age, health or other personal circumstances of that person; or

e) the extradition is requested pursuant to a final judgment rendered in the absence of the convicted person who, for reasons beyond his control, has not had sufficient notice of the trial or the opportunity to arrange for his defense and he has not had or will not have the opportunity to have the case retried in his presence.

፫/ አሳልፎ የመስጠት ጥያቄው ውድቅ የተደረገው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሀ) ወይም (ሠ) ወይም ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሐ) ወይም (ሠ) መሠረት ከሆነ ግለሰቡ ለጥያቄው መነሻ በሆነው ወንጀል እንዲከሰስ ለማድረግ ጉዳዩ አግባብ ላለው ባለሥልጣን እንዲተላለፍ ይደረጋል::

## ፵፮. አሳልፎ የመስጠት ቀላል ሥርዓት

ተላልፎ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበት ሰው አግባብ ያለው ባለሥልጣን ፊት ቀርቦ ተላልፎ እንዲሰጥ በመደረጉ መስማማቱን በግልጽ ካሳወቀ አሳልፎ መስጠቱ ተጨማሪ ሥነ ሥርዓት መከተል ሳያስፈልግ ይፈቀዳል::

## ፵፯. የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍና ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄዎችን ስለማስተላለፍ

፩/ ማዕከሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በተመለከተ አግባብ ባላቸው የሌሎች አገሮች ባለሥልጣኖች የሚቀርቡ የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍና ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄዎችን የመቀበልና ለአፈጻጸማቸው አግባብ ላላቸው ባለሥልጣኖች የማስተላለፍ ሃላፊነትና ሥልጣን ይኖረዋል::

፪/ ጥያቄዎችና መልሶች ለማዕከሉ የሚላኩት በፖስታ ወይም ማዕከሉ ትክክለኛነታቸውን ሊያረጋግጥ የሚችልባቸውን የጽሑፍ ወይም ተመጣጣኝነት ያላቸውን ማቴሪያላዊ ማስረጃዎች በሚያስገኙ የተሻለ ፍጥነት ባላቸው ሌሎች መንገዶች ይሆናል::

፫/ ጥያቄዎችና አባሪዎቻቸው በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ መቅረብ ወይም ከአማርኛ ወይም የእንግሊዝኛ ትርጉማቸው ጋር ተያይዘው መቅረብ አለባቸው::

## ፵፰. የጥያቄዎች ይዘት

፩/ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ይዘት የሚከተሉትን መግለጽ አለበት:-

ሀ) ጥያቄውን ያቀረበውን ባለሥልጣን ማንነት፤

ለ) የምርመራውን፣ የክሱን ወይም የፍርድ ሂደቱን የሚያካሂደውን ባለሥልጣን ስም፤

ሐ) ጥያቄው የቀረበለትን ባለሥልጣን፤

3/ If extradition is refused on either of the grounds stated in paragraph (a) or (e) of sub-article (1) of this Article or paragraph (c) or (e) of sub-article (2) of this Article, the case shall be referred to the appropriate authority in order that proceedings may be instituted against the person concerned in respect of the offence which gave rise to the request.

## 46. Simplified Extradition Procedure

Extradition may be granted upon receipt of a request, without further formalities, provided that the person whose extradition is requested explicitly consents before the competent authority.

## 47. Transmission of Mutual Legal Assistance and Extradition Requests

1/ The Center shall have the responsibility and power to receive mutual legal assistance and extradition requests sent by competent foreign authorities with respect to money laundering and financing of terrorism, and it shall transmit them to the competent authorities for execution.

2/ Requests and answers shall be transmitted either by post or by other more rapid means of transmission that provides a written or materially equivalent record under conditions allowing the Center to establish authenticity.

3/ Requests and their annexes shall be made in Amharic or English or accompanied by a translation in Amharic or English.

## 48. Content of Requests

1/ Requests shall specify:

a) the identity of the authority requesting the measure;

b) the name and function of the authority conducting the investigation, prosecution or proceedings;

c) the requested authority;

መ) የጥያቄውን ዓላማና ማንኛውንም አግባብነት ያለው ተያያዥ መግለጫ፤

ሠ) ለጥያቄው ደጋፊ የሆኑ መረጃዎችን፤

ረ) የሚመለከተውን ሰው ማንነት ለመለየት የሚረዳ ማንኛውንም የሚታወቅ ዝርዝር መግለጫ፣ በተለይም የግለሰቡን ስም፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዜግነት፣ አድራሻና የሚገኝበትን ሥፍራ እና ሥራ፤

ሰ) የሚመለከተውን ሰው፣ የወንጀል መፈጸሚያ፣ ገንዘብ ወይም ንብረት ለመለየትና ለመከታተል የሚያስፈልግ ማንኛውንም መረጃ፤

ሸ) ወንጀሉን የሚያቋቁመውን የሕግ ድንጋጌ ይዘት፣ ወይም አግባብነት ያለው ከሆነ በወንጀሉ ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረውን ሕግና ወንጀሉ ሊያስከትል የሚችለውን ቅጣት የሚመለከት መግለጫ፤ እና

ቀ) የተጠየቀውን ድጋፍ ዓይነት የሚያመለክት መግለጫ::

፪/ የተወሰኑ የድጋፍ ዓይነቶችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለባቸው:-

ሀ) ጊዜያዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የሚጠየቅ ሲሆን የሚፈለጉትን እርምጃዎች የሚያመለክት መግለጫ፤

ለ) የመውረሻ ትዕዛዝ ለማስጠት የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን የዳኝነት አካላት በአገሪቱ ሕግ መሠረት ትዕዛዙን ለመስጠት የሚያስችሏቸውን መረጃዎችንና የመከራከሪያ ነጥቦችን የያዘ መግለጫ፤

ሐ) ጊዜያዊ እርምጃዎችን የሚመለከት ትዕዛዝ ወይም የመውረሻ ትዕዛዝ እንዲፈጸም የሚጠየቅ ሲሆን:-

(፩) የትዕዛዙን የተረጋገጠ ቅጅ እና በትዕዛዙ ውስጥ ያልተካተቱ ከሆነ ትዕዛዙን ለመስጠት ያስቻሉትን ምክንያቶች የሚያሳይ መግለጫ፤

(፪) ትዕዛዙ ተፈጻሚነት ያለውና መደበኛ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ያለመሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ፤ እና

(፫) አስፈላጊና የሚቻል ሲሆን በገንዘቡ ወይም ንብረቱ ላይ ሊቀርቡ የሚችሉ የሦስተኛ ወገን የመብት ጥያቄዎችን፤

d) the purpose of the request and any relevant contextual remarks;

e) the facts in support of the request;

f) any known details that may facilitate identification of the person concerned, in particular name, marital status, nationality, address and location and occupation;

g) any information necessary for identifying and tracing the person, instrumentalities, funds or property in question;

h) the text of the statutory provision establishing the offence or, where applicable, a statement of the law applicable to the offence and an indication of the penalty that can be imposed for the offence; and

i) a description of the assistance required.

2/ In addition, requests shall include the following particulars in certain specific cases:

a) in the case of requests for provisional measures, a description of the measures sought;

b) in the case of requests for the issuance of a confiscation order, a statement of the relevant facts and arguments to enable the judicial authorities to order the confiscation under domestic law;

c) in the case of a request for the enforcement of an order relating to provisional measures or confiscation:

(1) a certified copy of the order, and a statement of the grounds for issuing the order if they are not indicated in the order itself;

(2) a document certifying that the order is enforceable and not subject to ordinary means of appeal; and

(3) where necessary and if possible, any information concerning third-party rights of claim on the funds or property;

መ) ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄው በወንጀሉ የተፈረደበትን ሰው የሚመለከት ሲሆን የፍርድ ውሳኔውን ዋና ወይም የተረጋገጠ ቅጅ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔውን፣ ቅጣቱ የሚኖረውን ተፈጻሚነት እና ያልተፈጸመውን ቀሪ የቅጣት መጠን የሚያሳይ ማንኛውንም ሰነድ::

d) in the case of requests for extradition, if the person has been convicted of an offence, the original or a certified copy of the judgment or any other document setting out the conviction and the sentence imposed, the fact that the sentence is enforceable and the extent to which the sentence remains to be served.

**፵፱. ተጨማሪ መረጃዎች**

ማዕከሉ ወይም ጉዳዩን በማየት ላይ ያለው አግባብ ያለው ባለሥልጣን ትዕዛዙን ለመፈጸም የሚያስፈልግ ወይም የሚረዳ ሆኖ ሲያገኘው አግባብ ያለው የጠያቂው አገር ባለሥልጣን ተጨማሪ መረጃዎች እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል::

**49. Additional Information**

The Center or the competent authority handling the matter may request additional information from the competent authority of the requesting state if it appears necessary to execute or facilitate the execution of the request.

**፶. ሚስጥር ስለመጠበቅ**

ጥያቄው መቅረቡ ወይም ይዘቱ በሚስጥር እንዲያዝ በጥያቄው ውስጥ የተገለጸ ከሆነ ይኸው መከበር ይኖርበታል:: ጉዳዩን በሚስጥር መያዙ የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ወዲያውኑ ጠያቂው አገር እንዲያውቀው መደረግ አለበት::

**50. Requirement of Confidentiality**

Where a request requires that its existence and substance be kept confidential, such requirement shall be observed. If that is not possible, the requesting authorities shall be promptly informed thereof.

**፶፩. ጥያቄ ማስተናገድን ስለማዘግየት**

እንዲፈጸም የተጠየቀው እርምጃ ወይም ትዕዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ ባለ ምርምራ ወይም የክስ ሂደት ላይ በመሠረታዊ ደረጃ ጣልቃ የሚያስገባ ሲሆን ማዕከሉ ጉዳዩን የማየት ሃላፊነት ላለው ባለሥልጣን መምራቱን ሊያዘገየው ይችላል:: ይህንኑም ለጠያቂው አገር አግባብ ያለው ባለሥልጣን ወዲያውኑ ያሳውቀዋል::

**51. Delay in Complying with Request**

The Center may delay the referral of a request to the authority responsible for the execution of the request if the measure or order sought is likely to substantially interfere with an ongoing investigation or proceeding. It shall immediately so advise the competent authority of the requesting state.

**ክፍል ሰባት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**PART SEVEN**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**፶፪. የማስረጃዎች ተቀባይነት**

በዚህ አዋጅ መሠረት የተያዘን መረጃ የሚመለከት ሰነድ ወይም የሰነዱ የተረጋገጠ ግልባጭ ወይም የተረጋገጠ የኤሌክትሮኒክ ሕትመት በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ላለ ጉዳይ በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል::

**52. Admissibility of Evidences**

Any document or a certified copy of the document or a certified printout of any electronic record, relating to information kept pursuant to this Proclamation, shall be admissible as evidence in court proceedings.

**፶፫. ስለይርጋ ጊዜ**

በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል በፈፀመ ሰው ላይ የሚቀርብ ክስና የሚጣል ቅጣት በይርጋ አይታገድም::

**53. Period of Limitation**

Criminal action and penalty regarding a person who commits money laundering or financing of terrorism may not be barred by period of limitations.

**፶፬. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ለማውጣት ይችላል።

፪/ ማዕከሉ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**፶፭. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት**

፩/ አግባብ ያላቸው የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፬/፲፱፻፺፯ ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣሙ እስካልሆኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት ገንዘብ ወይም ንብረት ለማገድ፣ ለመያዝና ለመውረስ የሚሰጡ ትዕዛዞችን አፈጻጸም በሚመለከት ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

፪/ የአዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

**፶፮. የዳኝነት ሥልጣን**

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ወንጀሎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል።

**፶፯. የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

፩/ የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፦

ሀ) በወንጀል ድርጊት የተ ገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፯/፪ሺ፪፤ እና

ለ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፮፻፹፬።

**54. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Center may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

**55. Applicability of other Laws**

1/ The relevant provisions of the Revised Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence Proclamation No. 434/2005 shall, in so far as they are not inconsistent with the provisions of this Proclamation, be applicable with respect to the execution of orders of freezing, seizure and confiscation of funds and property in accordance with this Proclamation.

2/ The provisions of Proclamation No.652/2009 shall be applicable with respect to matters not covered under this Proclamation.

**56. Jurisdiction**

The Federal High Court shall have first instance jurisdiction over offences stipulated under this Proclamation.

**57. Repealed and Inapplicable Laws**

1/ The following are hereby repealed:

a) the Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No. 657/2009; and

b) Article 684 of the Criminal Code.

፪/ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩)(መ) ድንጋጌ ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፶፰. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2/ The provisions of Article 5(1)(d) of the Anti-Terrorism Proclamation No. 652/2009 may not be applicable with respect to criminal offences of financing of terrorism.

58. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 4th day of February, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት